


አቤቱ ሞትህንና ልዩ ትንሣኤህን እንናገራለን እንመሰክራለን ።

# ትንሣኤ



ክርስቶስ ስለበደላችን መ
ከራ መስቀልን ታገሠ በእ
ርሱ ግርፋትና ሞት የአዳ
ም ልጅ ሁሉ ወደ ቀደመ
ክብሩ ተመለሰ ። (፩ኛ ጴ
ጥ፡፪ ፡ ፳፬-፳፭ )

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስ
ቶስ መስቀል በቀር ሌላ
ትምክህት ከእኔ ይራቅ ።
(ገላ ፡፮ ፡ ፲፬ )

«. . . . . ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸከመ ከአመፀኞችም ጋር ተቈጠረ ።እርሱ ግን ግፍን አላደረገም ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም ።» ኢሳ ፶፫ ፡ ፬ - ፲፪

www.ethiopianorthodox.org

ሚያዝያ ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

“ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ “ትንሣኤ” ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ራደ አስረስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

## ማውጫ

ገጽ

አርእስት
ደብዳቤዎች ........................ ፩
የክርስቶስ ትንሣኤ የመዳናችን ፍጻሜ........................ ፪
የመከራ ሳምንት........................ ፫
ፍጥረታት ሁሉ ያመሰግኑታል........................ ፬
የወይዘሮ አየለች ወ ሚካኤል ዜና ዕረፍት........................ ፭
የኩላሊት በሽታ........................ ፮
ኢየሱስን እንፈልጋለን........................ ፯
የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ........................ ፰
ምን እንርዳዎ? ........................ ፲
በዚያ ጻድቅ ሰው ላይ ክፉ አታድርግ ........................ ፲፪
ጸሎተ ሐሙስ ........................ ፲፬
ጴጥሮስ በስቅለት ሌሊት........................ ፲፭
ክርስቲያናዊ ጋብቻ ........................ ፲፮
ሰባት ዓመት እንደ አንድ ቀን ........................ ፲፯
ማርቆስ ሐዋርያ ........................ ፳
የሃምሳ ስድስት ዓመት ጋብቻ ........................ ፳፪
መልአከ ኃይል ኃይለ ሥላሴ ........................ ፳፫
በጎጃም ክፍለ ሀገር ስለሚገኙ ብሔረ ሰቦች ........................ ፳፬
ትምህርተ ግእዝ ........)

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የአባታችን የአቡነ ተክለሃይማኖት በዓል በሚከበርበት ጊዜ አልለይም የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አገልግሎት በሰበካ ጉባዔ አሳሳቢነት በሕዝቡ ትብብር እየተስተካከለ ነው ግን ስርክ የሚቀደስበትና ለአገራችን ሰላምና ጤና የሚጸለይበት እንዲሁም ብዙ ሕመምተኛ የሚፈወስበት ትልቁ ገዳም ደብረሊባኖስ ያለመብራት መገልገሉ በጣም አሳዝኖኛል ።

ከ50 ዓመት በፊት በዲናሞ የሚሠራ መብራት መኖሩን ሰምቻለሁ በበዓል ጊዜ ከ25-30 ሽህ የሚሰበሰበው ምዕመን እንኳን ቢጠየቅ ከ1-10 ብር ለማዋጣት ሁሉም ደስተኛ ነው ።

ታኅሣሥ 24 ቀን 74 ዓ.ም. ሄጄ ስለነበር ደስ እያለኝ እስከ ብር 500 ለመክፈል በጽሑፍ ለመጋቢው ገልጬ ነበር እሳቸውም ሐሳቤን በመደገፍ ከዚህ የበለጠ ከፍተኛ ገንዘብ ለመክፈል ቃል የገቡ ስለአሉ ይታሰብበታል ብለውኛል ይህንኑ ስንነጋገር የሰሙ አንድ የሲቪል ባለሥልጣን ሰምተው የንግሡ ዕለት ታቦቱ ዞሮ ሲገባ ወደ ፓትርያርኩ አቀርብሕናሐሳብህን ትገልጻለህ ብለውኝ ታቦቱ ዞሮ ከገባ በኋላ የሙዳይ ምፅዋት ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ ስለሆነ ትንሽ ጊዜ ቆየኝ ስላሉኝና እኔም መኪና ሊያመልጠኝ ስለሆነ ሳንነጋገር ሄጃለሁ ለዚህ በጎ ተግባር የማይተባበር ምእመን ስለሌ አትሳል ከተሳልክ ስዕለትህን አታቆይ የሚል የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስላለ ለሌላ ጉዳይ ሳይሆን የመብራቱ ሥራ ቢጀመር ዕለቱን የምከፍል ስለሆነ ልዑል እግዚአብሔር ሐሳቤን እንደሚፈጽምልኝ እመኛለሁ ።

ከምዕመናን አንዱ

“ከሞጆ ምእመናን አንዱ” በማለት ይህን ደብዳቤ የጻፉልን ክርስቲያን ስምዎን ለመግለጥ ስላልፈለጉ ይመስለናል “ከምእመናን አንዱ” በማለት የጻፉልን ። በደብዳቤዎ የተገለጸው ሐሳብ እጅግ ጠቃሚና ቤተ ክርስቲያን ከእውነተኞች ተከታዮችዋ የምትፈልገው የእምነት መግለጫ ነው ።

ስለሆነም የገዳሙ አስተዳዳሪዎችና ሌሎችም ምእመናን እንደ እርስዎ እንዲያስቡበት ስለሚያነቃቃ ሐሳብዎን በሙሉ በዚህ እትም አውጥተነዋል ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጤና ለሁላችሁ ይሁን ልዑል እግዚአብሔር ሰላምና ጤና ሰጥቶኝ በመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቼና እኅቶቼ ከሆናችሁት ከእናንተ ጋር ስተዋወቅ ሃይማኖቴ እንደ ምሰሶ ከሕይወቴ ጋር ተተክላ እንደማትነቀል ፈጣሪዬ የምሕረት ፊቱን ወደ እኔ ስላዞረልኝ ደስታዬ ፍጹም ነው ።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መልእክትና ዜና ስከታተል ብቆይም አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ በዚች ደብዳቤ ከእናንተ ጋር ስገናኝ ሐሳቤን በአጭሩ እገልጻለሁ ።

ብዙ ጊዜ በመጽሔት በጋዜጣና በመሳሰሉት የመገናኛ ዘዴዎች ስለቤተክርስቲያን ታወሱናላችሁ ፣ እንደ አጋጣሚ ጥር 7 ቀን 74 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥቼ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የሥላሴን በዓል አከብሬአለሁ ። ታዲያ ጥር 6 ቀን ለ7 አጥቢያ 74 ዓ.ም በካቴድራሉ ውስጥ ያየሁትን ድርጊት ብገልጽላችሁ ለወደፊቱ ርማት ለማድረግ ይረዳ ይሆናል በማለት ይህችን የጥያቄ ደብዳቤ ለመጻፍ አሰብሁ ።

በተጠቀሰው ዕለት ጥር 6 ለ7 ሐሙስ ለዓርብ አጥቢያ ማለት ነው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሥርዓተ ማኅሌት በደብሩ ካህናት ተጀመረ ። ምእመናንም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መግባት ጀመሩ መሣሪያ የያዙ ሁለት ዘበኞች ነበሩ ብዙ ምእመናን በጸሎት ላይ ይታያሉ ማኅሌቱ ደመቀ በዓሉን ለማክበር የመጡ ምእመናንም በማኅሌቱ ዙሪያ ሆነው የዜማውን ቃና በጆሮአቸው በማዳመጥና የካህናቱን ውዝዋዜ በዐይናቸው በመመልከት በተመስጦና በመንፈሳዊ ደስታ ላይ ሳሉ እነዚያ ሁለት ዘበኞች አንዳንድ ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያን ውጡ ማለት ጀመሩ ። እኔም በቆምኩበት አካባቢ በጸሎት ላይ የሚታዩ ምእመናን ነበሩ በመካከላችንም አንድ አዳፋ ልብስ የለበሱ አባት ይጸልዩ ነበር ዘበኞቹ ወደ እርሳቸው በመቅረብ ክርክር ጀመሩ ለምን እንደሚጨቃጨቁ ጠየቅናቸው ። ዘበኞቹ የምእመናኑ ጫማ ይጠፋል የሚወስዱትም እንደእነዚህ አይነት ሰዎች ናቸው አሉን እኛም እኒህ ሽማግሌ ምንም ገንዘብ አግኝተው ልብስ ባይለብሱም ደሃ ናቸውና ሌባ ይሆናሉ ከቤተ ክርስቲያን ይውጡ መባል የለባቸውም በማለት ገላግለን ለጊዜው እንዳይወጡ አደረግን ። የእኔ ጥያቄ ቤተ ክርስቲያን የቆመችው ለድሆች ነው ? ወይስ ለባለጸጎችና ያጌጠ ልብስ ለለበሱ ? እየሰከሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትንና የሰው ገንዘብ የሚያነሡትን ለመቆጣጠርም ሆነ ሥነ ሥርዓት ለማስከበር ተቆጣጣሪዎች መኖራቸው መልካም ነው ። ግን በዚያ ዕለት እንደተመለከትኩት ከሆነ ዘበኞቹ ደሃ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳታስገቡ የተባሉ ይመስላል ። ስለዚህ ትንሣኤ ምን አስተያየት አለው ?

ዲያቆን በላይ ጸጋዬ
አርሲ አሰላ መድኃኔ ዓለም ።

ዲያቆን በላይ ጸጋዬ ስለጥያቄህና ስለ ሰላምታህ እናመሰግናለን የሃይማኖትህን ጽናት በደብዳቤህ ስለተረዳን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን እንዲሁም የምታገለግላቸውን ምእመናን በሃይማኖት እንድታጸናቸው እንመኛለን ። በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን የቆመችው ለድሃ ወይም ለባለ ጸጋ ብቻ አይደለም

ወደ ገፅ ፲፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርዕሰ አንቀጽ

# የክርስቶስ ትንሣኤ የመዳናችን ፍጻሜ

የክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስትና እምነታችን ልብና ማእከል ነው ። የመዳናችን ፍጻሜ የተረጋገጠው በመ
ስቀል ላይ የተከፈለው የመሥዋዕትነት ሥራ ሁሉ ፍጹም የሆነው መድኀን ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በመ
ነሣቱ ነውና ።
መድኃኒታችን ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ለኀጢአታቸው ይቅርታን
አግኝተዋል ። "ክርስቶስ ስለበደላችን ሞተ ሊያጸድቀንም ተነሣ" ተብሎአልና ። (ሮሜ. 4. 25)
የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ለማስተማር ብቻ አልነበረም ። ግን ለመሞት ሞቶም ለመነሣት
በትንሣኤውም የአዳኝነቱን ኃይልና ዘለዓለማዊ ሕያውነቱን ለመግለጥ ነበር ። ትንሣኤው ለፍጹም አምላክነቱ
ምስክር ሆኖአል ። "በራሴ ብቻ ሥልጣን ተነሣሁ" ነፍሴን እነሣት ዘንድ እሰጣለሁ ። ... እኔ በፈቃዴ እሰጣ
ታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም ። ልሰጣት ሥልጣን አለኝ ። ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ" በማለት
ራሱ ጌታችን ስለ ራሱ እንደተናገረ ሌላ አስነሽ ኃይል ሳይሻ በመለኮታዊ ሥልጣኑ ተነሥቷልና (ዮሐ. 10፡
17-18) ።
መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ በፈቃዱ እንደሞተ በሥልጣኑ ተነሥቷል ። ሞቱም በራሱ በደል አልነበረም ።
እርሱ ንጹሐ ባሕርይ ነውና ። ይሁን እንጂ ስለ ሰዎች በደል ተላልፎና ለኀጢአተኞች ቤዛ ሆኖ ሞቷል ። ግን
በሰዎች ኀይል ድል ሆኖ አልሞተም ። ቅዱስ ኃያል ፤ ቅዱስ ሕያው ነውና ።
በክርስቶስ ሞት የተገኘው ደኅንነታችን በትንሣኤው ተረጋግጦአል ። ክርስቶስ እንደተነሣ ሙታን ሁሉ
ይነሣሉና።ይህንም ለማረጋገጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚከተለውን ጽፎአል ። "ክርስቶስ ለሞቱት ሁሉ
በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል...." ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ
(1 ቆሮ 15፡20-21) ። ነገር ግን ትንሣኤያቸው የተለያየ ይሆናል ። በአካል የመነሣቱ ሁኔታ አንድ ሲሆን በክብር
መለያየት ይኖራል ። ለምሳሌ ምእመናን የክብር ትንሣኤን ሲነሡ ኢመእመናን የኀሣር ትንሣኤን እንደሚነሡ
ተጽፎአልና (ዮሐ. 5. 29)
በክርስቶስ ትንሣኤ የሞት ኀይል ድል ሆኗል ዛሬ እውነተኞች ክርስቲያኖች ሞትን አይፈሩም ። ይልቁ
ንም "ኃጢአትን እንጂ ሞትን አትፍሩ" እያሉ ለሌሎች ያስተምራሉ ። እንደ ጳውሎስ "ከክርስቶስ ጋር ለመ
ኖር ከዚህ ዓለም በሞት እንድለይ እፈልጋለሁ" ይላሉ ። ከዳዊትም ጋር "በሞት ጥላ ወንዝ እንኳ ብሄድ ክፉውን
አልፈራም አንተ ከእኔ ጋር ነህና" እያሉ ይዘምራሉ (መዝ. 22. 4)
ስለዚህ ከክርስቶስ ትንሣኤ ወዲህ ሞት ከሕይወት ወደ ሕይወት የሚያሸጋግር ድልድይ እንጂ የሕይወት
ፍጻሜ አይደለም ። በማንኛውም ሃይማኖት የተስፋ ትንሣኤ አለ ። ስፈ ትምህርትም ስለ ትንሣኤ ይሰጣል ። ከሁ
ሉም በላይ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ ትምህርተ ትንሣኤና ተስፋ ትንሣኤ እጅግ ጎልተው ይነገራሉ ። ያለ ጥር
ጥርም ይታመናሉ ። ምክንያቱም ክርስቶስ በእውነት ተነሥቶአልና ። ተነሥቶም ለሚያምኑበት ተገልጦአልና ።
ስለዚህም የወንጌል ትምህርት የሐዋርያት ስብከት በክርስቶስ ትንሣኤ ላይ ተመሥርቶአል ። የቤተ ክርስቲያ
ንም ህልውና ሊጸና የቻለው በትንሣኤው እርግጠኛነት ነው ።
የክርስቶስን ትንሣኤ ለማመን የተጠራጠሩ አንዳንድ መናፍቃን ነበሩ ። ግን ጁሊየስ ቄሣር ወይም ታላቁ
እስክንድር በዚህ ዓለም እንደኖሩ ከሚቀርበው ማስረጃ ይልቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ እንደ
ተነሣ የቀረቡት ማስረጃዎች በይበልጥ ተቀባይነትና ታማኝነት አላቸው ። ለምሳሌ ከተነሣ በኋላ ለተለያዩ
ሰዎች ለአሥራ አንድ ጊዜ ያህል በግልጥ ታይቶአል ። ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተመግቦአል ። እነ ቶማስ የተወጋ
ጎኑን ዳስሰውታል ። ቅዱሳት አንስት (ሴቶች) እግሩን በመንካት ሰግደውለታል ። ለደቀ መዛሙርቱ በጉባዔ ኪዳ
ንና ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን አስተምሮአል ( የሐዋ.1፡1-5)
ሐዋርያት ፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ ጊዜ እጅግ ፈርተው ነበር ። "እነሣለሁ" በማለት የነገራ
ቸውን ትምህርት በመዘንጋት ሕይወቱ በመስቀል ላይ እንደአበቃ አስበው ነበር ። ግን ከሙታን ተለይቶ ተነሥ
ቶ ካዩት በኋላ ስለትንሣኤው ሲሰብኩ አልፈሩም ። ምስክርነታቸውንም የቄሣሮች ትግርሞት ሊያስተባብለው
አልቻለም ። የእሳት ወይም የስለት ሞት አልገታውም ። ትንሣኤው እውነት ነውና ።
እኛም ዛሬ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን ። ስለ እኛ በመስቀል ላይ የሆነ ሞቱን እንናገራለን ።
ትንሣኤውንም እናምናለን ፤ የምናምነውንም እንመሰክራለን መዳናችን በትንሣኤው ተረጋግጦአልና ።



# የመከራ ሳምንት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአ
ዳምና ለልጆቹ ደኅንነት ሲል በአይሁድ
አደባባይ ቆሞ የተወቀሰበት ወንጀል
ሳይኖርበት እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ
የሞትን ፍርድ የተቀበለበትና አዳምን
ከነልጆቹ ከመከራ ነፍ ከሞተ ነፍስ ያዳ
ነበት ሳምንት እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶ
ክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጠራር
ሰሙነ ሕማማት ይባላል ። የመከራ
ሳምንት ማለት ነው ። እንደ ሌሎች አብ
ያተ ክርስቲያንም "ቅዱስ ሳምንት"
ይባላል ።
ይህ ሳምንት ከሆሣዕና እሁድ እስከ
ቅዳሜ ሥዑር ባሉት ዕለታት ይጠሰ
ናል በነዚህ ዕለታት መድኃኒታችን ኢ
የሱስ ክርስቶስ የተለያዩ ዐበይት ጸዋ
ትወ መከራን ተቀብሎ የሰዎችን መከራ
አስወግዶአል ። እርሱ ተሠቃይቶና ታ
ምሞ የሰዎችን ሥቃይና ሕማም ያራ
ቀው የሰው ሕሊና ሊደርስበት በማይ
ችል የጥበብና የትሕትና ምሥጢር
ነው ።
ዲያብሎስ የተከለከለውን ቅጠል
ብትበላ አምላክ ትሆናለህ ብሎ አዳምን
የመከረው ሥጋን በመቃብር ነፍስን
በገሃነም ተቆራኝቶ ለመኖር አስቦ ነበር
ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ግን የመከረ
ባቸው ነፍስና ሥጋን ተዋሕዶ ምክሩን
ሻረበት ቁራኝነቱን አጠፋበት ። ስለዚ
ህም "ሰይጣን በተንኮሉ በሥጋ ከይሲ
(በእባብ አካል) እንደ ተሠወረ እኛም
ከፍዳ መዳናችን ቃለ እግዚአብሔር በባ
ሕርያችን በመሠወሩና ሥጋን በመዋሐ
ዱ ሆነ ።" ተብሎ ተጽፎአል (መቅ.
ወን)
ሕማምና ሞት መከራና ሥቃይ የባ
ሕርዩ ያልነበረ ቃለ እግዚአብሔር ወል
ድ መከራና ሥቃይ ሕማምና ሞት የባ
ሕርዩ የሆነ ሥጋን ተዋሐደ ። በሥጋ
በምድር ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስ
ት ወር ያህል ተመላለሰ ወንጌልን አስ
ተማረ ከዚህ በኋላ የሆሣዕና ዕለት እ
ሁድ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳ
ሌም በድል አድራጊነት ገባ ሕፃናትና
ሽማግሎች በዝማሬ ተቀበሉት በማግ
ስቱ ሰኞ በቤተ መቅደስ ይሸጡና ይለ
ውጡ የነበሩትንና ሕገ ወጥ ሥራቸውን
ነቀፈ ከቤተ መቅደስም አባረረ ። ከዚ
ህም ሌላ ፍሬ ያልነበራትን በለስ ረገ
መ በበለስ አንጻር ኃጢአትንም ረገመ
(አስወገደ) ሰኞ የተረገመችው በለስ
ማክሰኞ ደርቃ ተገኘች የበለስ መረገ
ምና መድረቅ ከክርስቶስ ሕማምና ሞት
በኋላ የቀደመው የአዳም ኃጢአት በፍ
ዳ የማያስይዝ መሆኑን ያመለክታል ።
ማክሰኞ ስለ ግብር አከፋፈል ስለ
ትንሣኤ ሙታንና የዳዊት ልጅ የሚ
ባል ማን ስለመሆኑ ከጸሐፍትና ፈሪሳ
ውያን ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሰጠ ጸሐ
ፍትንና ፈሪሳውያንንም ስለ ተንኮላ
ቸው ገሠጻቸው ማቴ. 23 ማርያም እንተ
ዕፍረት የተባለችው ሴት በስምዖን
ቤት ሽቱ የቀባችውና ይሁዳም ጌታን
ለማስያዝ የተመሳጠረው በዚሁ ዕለት
ነው ።
ረቡዕ አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስን ለማስገደል ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ
እንዴት እንደሚይዙት ማን እንደሚያ
ስይዛቸው ባደረጉት ጽኑዕ ምክር ለክፉ
ሥራቸው ተባባሪ ያደረጉት የአስቆሮ
ቱን ይሁዳ ነበር ።
ሐሙስ ፡- ለመጨረሻ ጊዜ የፋሲካን
ራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በላ ከራት
በኋላ የኦሪቱን ሥርዓተ መሥዋዕት
ሽሮ አዲስ ሥርዓተ ቁርባን ሠራ ። ከዚ
ያም በኋላ በጌቴ ሴማኒ ጸለየ ደቀ መዛ
ሙርቱም ተግተው እንዲጸልዩ አስተ
ማረ ። ወዲያውም ይሁዳ የአይሁድን
ጭፍሮች እየመራ አምጥቶ ጌታን አስ
ያዘው ።
ዓርብ ፡- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ እስከ መስቀል ሞትና መቃብር
ድረስ ያሉትን ጸዋትወ መከራ ተቀበለ ፤
በመስቀል ላይ ሳለ ሰባቱን አጽርሐ መ
ስቀል (ነገራተ መስቀል) ተናገረ ሰባ
ቱን ተአምራት አደረገ ሰባቱ አጽርሐ

መስቀል ፡-


ክርስቶስ ስለበደላችን ተሰቀለ

1ኛ የሚያደርጉትን አያውቁምና
አባት ሆይ ይቅር በላቸው ሉቃ. 23፡34
2ኛ አምላኪየ ሆይ ለምን ተውኸኝ
ማቴ. 27 ፡ 46
3ኛ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትኖራለህ
ሉቃ. 23 ፡ 43
4ኛ እነሆ ልጅሽ እነሆዋት እናትህ
ዮሐ. 19፡26
5ኛ ጸማዕኩ (ተጠማሁ) ዮሐ. 19፡29
6ኛ አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደ
ራ እሰጣለሁ ሉቃ. 23፡46
7ኛ ወይቤ ተፈጸመ ኩሉ (ሁሉ ተፈ
ጸመ) ዮሐ. 19፡30 ናቸው ።
ሰባቱ ተአምራት የሚባሉትም
ሀ የፀሐይ መጨለም ፤ ለ የጨረቃ ደም
መሆን ፤ ሐ የከዋክብት መውደቅ ፤
መ የመቃብራት መከፈት ፤ ሠ የሙ
ታን መነሣት ፤ ረ የአዕባን መከፋፈል ፤
ሰ የመንጦላዕተ ቤተ መቅደስ ከሁለት
መከፈል ናቸው ማቴ. 27፡51-52 ፤
ሉቃ. 23፡45 እነዚህ ተአምራት የተፈ
ጸሙ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለሰ
ዎች ቤዛ ሆኖ በተሰቀለና በሞተ
ጊዜ ነው ከዓርብ 11 ሰዓት እስከ እሁድ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሮአል



www.ethiopianorthodox.org

# ፍጥረታት ሁሉ ያመሰግኑታል

የክብርና የምስጋና ባለቤት የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዚህ ዓለም የመጣው በኩነኔ የተያዙትን ነፃ ለማውጣት ፡ በጠላት አገዛዝ ሥር የወደቁትንም ከጠላት አገዛዝ ለማላቀቅ ሲሆን ስለነፃታቸው የሚደረግላቸውን የማያውቁ አይሁድ መድኃኒታቸውን ለማጥፋት ያላደረሱበት መከራ የለም ።

ከዚህም ሌላ የሚያደርገው ተአምራት እንዳይታወቅ አምላክነቱ እንዳይነገር የፈወሳቸው በሽተኞችም የተደረገላቸውን እንዳያወሩ ይከለክሉ ነበር ።

ይሁን እንጂ ፈሪሳውያን ማንኛውንም ጥፋት ቢያደርጉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምስጋና ባለቤት ነውና ከመመስገን የተለየበት ጊዜ የለም ፡ መላእክት በሰማይ ፡ የምድር ፍጥረታት በምድር ዘወትር ያመሰግኑታል ።

የክብር ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየዓመቱ በኢየሩሳሌም የሚከበረውን በዓል ለማክበር በክብርና በድል አድራጊነት ወደኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ማንም ሳያስልፋቸው ፡ እንዲቀበሉትም ቅስቀሳ ሳይደረግላቸው በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ሕዝብ የዘንባባና የወይራ ዝንጣፊ ይዘው በመዝሙርና በዕልልታ ተቀብለውታል ። ሲቀበሉትም ከማንም ሳይማሩ ፡ ያስጠናቸውም ሳይኖር የሚከተሉትን ቃላት በማዜምና በታላቅ ድምፅ በመናገር ነበር ።

"ሆሳዕና በዓርያም" መድኃኒት በሰማይ !

"ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ" ምስጋና ለክርስቶስ"!

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው ።

"ሰላም" በምድር

የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና ጌትነት የሚገልጡት እነዚህ እረፍተ ነገሮች ሲነገሩና ድል አድራጊነቱንም ሲያበስሩ የነበሩት ሕፃናትና አራጋውያን ናቸው ።

ይሁን እንጂ ክርስቶስ እንዳይመሰገን ፡ የክርስቶስ ድል አድራጊነትና ጌትነትም እንዳይነገር ዘወትር ይጥሩ የነበሩ አይሁድ ይህን ዓይነት አቀባበልና ምስጋና ባዩና በሰሙ ጊዜ ፈሪሳውያን የካህናትም አለቆች ቀደም ሲል እንዳይመሰገን የሚያደርጉት ሙከራ አለመሳካቱን አይተው በቅንዓት ተቃጠሉ ።

ስለዚህም ሌላ የሚያደርጉትን ነገር ስላጡ ወደጌታችን ቀርበው "እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን አትሰማምን? አሉት" ጌታም እሰማለሁ ፡ ግን ከሕፃናት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ የሚለውን ቃል ከቶ አላነበባችሁምን ? እነዚህ ሕፃናት ዝም ቢሉ ድንጋዮች ጮኸው ይናገራሉ አላቸው ማቴ. 21 ፡ 15 ፡ መዝ. 8፡2 ፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይናገራሉ ማለቱ ያለ ምክንያት አይደለም በሕፃናትም ሆነ በሽማግሌዎች አንደበት መመስገን እንደሚገባው አስቀድሞ በትንቢት የተነገረውን እንዲያስተውሉ ለማድረግና ራሳቸው ፈሪሳውያንና የካህናት አለቆች በትዕቢት ተውጠው ለምስጋና አፋቸውን ቢዘጉም ድንጋዮች ለጌታ ምስጋና መናገር እንደሚችሉ ሲነገራቸው ነው ።

አዎ በእርግጥም ለእግዚአብሔር የማሳነው ነገር የለም ። ለምስጋና የተፈጠረው ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ ዘንግቶ በትዕቢትም ተውጦ ባያመሰግን ሌሎቹን መናገር የማይችሉትንና የተናቁትን ግዑዛን ፍጥረቶች ለምስጋና ያቆማል ። መጥምቁ መለኮት ዮሐንስ ሰዎችን በንስሐ ለማዘጋጀት እየዞረ በሚያስተምርበት ጊዜ አይሁድ ከአብርሃም በመወለዳቸው ብቻ ያለምንም ቅን ተግባር በመታበይ ስለአስቸገሩት "እግዚአብሔር ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ማስነሣት ይችላል" ሲል መልሶላቸው ነበር ። ማቴ. 3፡9 በእርግጥም ተስፋ የተሰጣቸው፡ትንቢትም የተነገረላቸው አይሁድ በተስፋው መሠረት ትንቢቱን ለመፈጸም የመጣውን የዓለም መድኃኒት ክርስቶስን ባይቀበሉና ባያመሰግኑም በእነርሱ ቦታ ተስፋ ያልተሰጣቸው ፡ ትንቢትም ያልተነገረላቸው አሕዛብ አመስግነዋል ። የተስፋው ቃል ያልተነገረላቸው አሕዛብ አመስግነዋል ። የተስፋው ባለቤትም ሆነዋል ።

እኔሆ በሆሣዕና ዕለት የተስፋ ባለቤቶች የነበሩት አይሁድ ለማመስገን ዝም ሲሉ በማዕዶተ ዮርዳኖስ የነበሩ አሕዛብና የሰማርያ ሰዎች ሆሣዕና በአርያም ምስጋና ለዳዊት ልጅ እያሉ ከአንዳንድ እውነተኞችና አስተዋይ ከሆኑ አይሁድ ጋር አመስግነዋል አይሁድ ክርስቶስ ድውዮችን በፈወሰ ፡ ሙታንን ባስነሳ ፡ የተራቡትን ባጠገበ ከከተማችን ውጣልን እያሉ ሲጮሁ ፡ የተናቁትና የተስፋው ባለቤት ያልሆኑት የሰማርያ ሰዎች በከተማቸው ክርስቶስ እንዲቆይ ፡ በሽተኞቻቸውንም እንዲፈውስላቸው ይለምኑት እንደነበረ በወንጌል ተጽፎአል ።

እንግዲህ ሰዎች ዝም ቢሉ ሌሎች ክርስቶስን እንደሚያመሰግኑ በመጀመሪያ በዕለተ ሆሣዕና በተአምራታዊ ኃይል ሕይወት የሌላቸው ሆሣዕና በአርያም ብለው ማመስገናቸውን ያመለክታል በሌላ በኩል ደግሞ ክብርና መዐርግ ያላቸው ፈራሳውያን ለማመስገን ሲከሩ በአእምሮም ሆነ በመዐርግ እንዲሁም በዕድሜ ዝቅተኞች የሆኑ ሕፃናት በታላቅ ድምፅ ማመስገናቸውን ያሳያል ።

በአጠቃላይ አሳብ ለጌታ ክብር ምስክሮች የሚሆኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ፍጥረቶች ሁሉ አምላክነቱንና ክብሩን ይመሰክራሉ ።

ነቢዩ ዳዊትም ግዑዛን ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ ሲገልጽ "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ። የሰማይም ጠፈር የእ



ጁን ሥራ ያወራል ። መዝ. 18 ፡ 1 ብሏል ። በማንኛውም ነገር ሁሉ የተፈጠሩ ፍጡራን እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባቸውና እንደሚያመሰግኑም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ተገልጾ ይገኛል ።

ስለዚህም ለምስጋና የተፈጠረው የሰው ልጅ አንደበት በትዕቢት ተሞልቶ ማመስገኑን ቢተውም እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጡራን እንጨቱና ደንጋዩ ተራራውና ሸንተረሩ ወንዞችና ባህሩ ያመሰግኑታል ።

ስለዚህ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን አውቀን ብናመሰግነው ክብሩና ጥቅሙ የራሳችን መሆኑን አውቀን እናመሰግነው ።

ተስፋ ጥሩነህ

# የወ/ሮ አየለች ወ/ሚካኤል ዜና እረፍትና አጭር የሕይወት ታሪክ



ወ/ሮ አየለች ወ/ሚካኤል የቡልጋ ተወላጅ ከሆኑት ከአባታቸው መምሬ ወልደ ሚካኤል ወ/ሰንበትና ከእናታቸው ወ/ሮ ንጋትዋ ወ/መስቀል በአርሲ ክፍለ ሀገር በጭላሎ አውራጃ በሂጦሳ ወረዳ ልዩ ስሙ ቦሩ ጃዊ ከተባለው ሥፍራ በ1911 ዓ.ም. ሕዳር 21 ቀን ተወለዱ ።

በኋላም በሸዋ ክፍለ ሀገር በአዲስ አበባ ከተማ ከአጋፋሪ ተፈረደኝ ባንትይለኩ ጋር ጋብቻቸውን በሕግ መሠረቱ ፡ ከአጋፋሪ ተፈረደኝ ጋር ከተጋቡበት ጊዜ ጀምሮ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ በመባባል በሰዎች ዘንድ በሚያስቀና አኗኗር ላይ እንዳሉ አጋፋሪ ተፈረደኝ የሰዎች ልጆች ተምረው ተመራምረው የአምላካቸውን ፈለግ እንዲከተሉ ባላቸው ምኞት ትምህርት እንዲማሩ አድርገው ፈደል በመቁጠር ዳዊት ለመድገም በቁ ። ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው»በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት በ1960 ዓ.ም. በሥጋ ወደሙ ተወሰኑከዚህም ጋርለተራብ በማብላት ፡ለተቸገረ ገንዘብ እህል በመስጠት ለታረዘ ልብስ በማልበስ ክርስቲያናዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

. በሌላ በኩል በጻድቃን ሰማዕታት ፡ በቅዱሳን መላእክት ስም የሰጠ በስማቸው ዝክር የዘከረ የዘላለማዊ ዋጋን እንደሚያገኝ በማመንበየዓመቱ፡ታህሣሥ 19ቀንየቅዱስገብርኤል ዝክርበመዘከር ካህናቱንእየጠሩ ሲጋብዙበተለይምይበሉት አጥተው የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት ኖረዋልወ/ሮ አየለችና አጋፋሪተፈረደኝባንትይለኩ በዚህ አይነት አኗኗር በቤት ውስጥ ሳይቸገሩ ወገኖቻቸውን እየረዱ፡በውጭ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይረዳቸው ዘንድ ችግረኞችን እየረዱ ሳሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው" መሬት ነህ ወደ መሬትም ትመለሳለህ" ተብሎ በተሰጠው አምላካዊ ቃል መሠረት አጋፋሪ ተፈረደኝ ነሐሴ 17 ቀን 1973 ዓ. ም. በ72 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።

ወ/ሮ አየለች ወ/ሚካኤል በባለቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ምክንያት በኃዘን ላይ ሳሉ ታህሣሥ 15 ቀን 1974 ዓ.ም. ከቀኑ 8 ሰዓት በተወለዱ በ63 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ተለይተዋል ።

ዘመድ አዝማዳቸው ና ቤተሰቦቻቸው በእንባ እየተራጩ ታህሣሥ 16 ቀን 74 ዓ.ም. የባለቤታቸው አጋፋሪ ተፈረደኝ ባንትይለኩ አስከሬን በአረፈበት በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ካቴድራል የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተጽጽሞአል።





አጋፋሪ ተፋረደኝና ወ/ሮ አየለች እነዚህ ነበሩ

## ጴጥሮስ በስቅለት....

ከገጽ ፳፪ የዞረ

ከትንሣኤ በኋላ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምሳ በልተው ሲያበቁ ስምዖን ጴጥሮስን የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?አለው ጴጥሮስም አዎ ጌታ ሆይ እንደምወደው አንተ ታውቃለህ ባለው ጊዜ ግልገሎቼን አሰማራ ጠቦቶቼን ጠብቅ ፡ በጎቼን አሰማራ በማለት ምዕመናንን በንቃትና በትጋት እንዲያስተምር አዝዞታል ዮሐ. 21. 15 - 17 ።

ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ የክርስቶስን ትእዛዝ ተቀብሎ የወንጌልን ቃላት ዞሮ አስተምሯል

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# የኩላሊት በሽታ

በአጠቃላይ የሰውነት ክፍሎች ውስጥ የአንዱ መታመም የመላው ሰውነት ጤና መቃወስ መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለዚህ አንድ ሰው የበሽታዎችን ምልክቶች ና ሁኔታዎች በመጠኑ ከተረዳ ጥንቃቄ ለማድረግም ሆነ ሕመሙ ወደ ተባባሰ ደረጃ ከመድረሱም በፊት ወደ ሕክምና ባለሙያዎች ለመቅረብ ችግር አይኖርበትም በዚህ አንጻር በአሁኑ ክፍል ስለኩላሊት ሥራና በሽታ በአጭሩ እና ያለን ።

አንዱ ኩላሊት በግምት 125 ግራም ሲመዝን በውስጡም የተለያዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ክፍሎች አሉት ። የሚሰጠውም አገልግሎት ማንኛውንም ነገር በማጣራት ለሰውነት ጠቃሚ የሆኑትን ሁሉ እንዳይበዙም እንዳያንሱም በማድረግ መጠናቸው ተጠብቆ በተስተካከለ ሁኔታ ጥቅም መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል ።

ለምሳሌ ፡- ውኃ በሰውነታችን ውስጥ ከበዛ አስፈላጊውን መጠን ብቻ ትቶ ትርፉን በሽንት መልክ ያስወጣል ። እንደዚሁም በሰውነታችን ውስጥ የጨው መጠን ከፍ እንዳይል በደም ውስጥም የስኳር መጠን ከፍ እንዳይል ይቆጣጠራል ። የደምን ዝውውር ብንመለከት የኩላሊትን ያህል ክብደት ካላቸው ክፍሎች ይልቅ በግምት አሥር ጊዜ ያህል ወደ ኩላሊት እንደሚጓዝ ይታወቃል ። በዚህ ዓይነት መንገድ በደም ውስጥ ያሉ ቆሻሻ ወይም የማይጠቅሙ ነገሮች ሁሉ ተጣርተው ንጹህ ደም በመላው ሰውነት እንዲዘዋወር ይሆናል ።

አንድ ሰው ኩላሊቱ ጤናማ ከሆነ በቀን ከ5 - 6 ጊዜ ያህል ይሸናል ። አልፎ አልፎም በሌሊት አንዴ ሊሸና ይችላል። መጠኑም በ24 ሰዓት ውስጥ ከ 1200 - 1500 ሚ. ሊ. ያህል ይሆናል ይህም ሲሆን ሰውየው ምንም ዓይነት የመሽናት ችግር ወይም የማቃጠል ስሜት አይኖረውም ይሁን እንጂ የሽንቱ መጠን እንደ የአካባቢው የአየር ጠባይ ፣ ሰውየው እንደሚወስደው የመጠጥ ብዛት ወይም ማነስ እንዲሁም በሌላ በሽታዎች እንደ ተቅማጥና ትውከት ባሉ ሁኔታዎች ሊለያይ ይችላል ።

እንግዲህ ኩላሊታችን ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች በትክክል የሚያከናውን ካልሆነ አንድ ዓይነት ችግር ወይም በሽታ አጋጥሞታል ማለት ነው። በሽታው ወይም ችግሩ የሚመጣው በተለያየ ዓይነት መንገድ ነው ።

ይኸውም የጉሮሮ አንዳንዴም የጆሮ ሕመም ሲኖር ፣ ጎጂ ባልሆኑ በአንጀት ውስጥ በሚኖሩ ባክቴሪያዎች አማካኝነት በሽንት መጠራቀም ምክንያት በሚፈጠሩ ጠጠሮች እንዲሁም ወደ ሌላ የሰውነት ክፍል ሊሰራጩ በሚችሉም ሆነ በማይሰራጩ እበጦች እባጮችና በአደጋ ምክንያት በኩላሊት ላይ ጉዳት ሲደርስ ነው ። አሁን የበሽታውን ሁኔታና የሚያሳየውን ምልክት አልፎ አልፎ እናያለን በጉሮሮ ሕመሞች ላይ ለምሳሌ በቶንሲል ሕመም ምክንያት ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች ይልቅ ኩላሊት በቶሎ ይጎዳል ጉዳቱም የሚደርሰው በሁለቱም ኩላሊቶች ላይ ነው ። ካሉት ክፍሎችም ውስጥ አንዳንዶቹ ወይም አብዛኞዎቹ የመሞት ዕድል ያጋጥማቸዋል ። ከዚያም የመቁሰልና የመላጥ ሁኔታ ይከተላል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተላጠውና የቆሰለው ይድንና ጠባሳ ይፈጥራል ። በሞቱት ሴሎችና በመበከሉ ምክንያት መግልም ሆነ ሌላ ዓይነት ፈሳሽ ይወጣል ። እንደዚሁም በጠባሳው ምክንያት በአካባቢው በቂ የደም ዝውውር ሲኖር ስለማይችል ተፈላጊ ሥራውን ለማከናወን የማያስችል ሁኔታ ያጋጥመዋል ።

ፈሳሹም ሆነ መግሉ ደግሞ በበኩሉ የማጣሪያ ቦታውን በመዝጋት ከፍተኛ ችግር ያስከትላል። ይህ ሕመም የሚያሳያቸው ምልክቶች ትኩሳትና ብርድ ብርድ የሚል ስሜት ራስ ምታት፣ መፍዘዝ ማቅለሽለሽና ማስታወክ ፣ የጀርባ ሕመም ድካም እንዲሁም የፊትና የእግር እብጠት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ምልክቶች ሁሉ ሳያሳይ በቁርጭምጭሚት አካባቢና በዓይን ቆብ ላይ መጠነኛ እብጠትና የፊት መገርጣት ብቻ ሊያሳይ ይችላል ። ይህ ዓይነቱ የኩላሊት በሽታ ከትልልቆቹ ይልቅ በብዛት የሚያጠቃው ወጣቶችን ሲሆን በይበልጥ በሕፃናት ላይ ይሆናል ።

ከላይ የጠቀስናቸው ባክቴሪያዎች በአንጀት ውስጥ ሲኖሩ ምንም ጉዳት አያስከትሉም ግን ከዚያ ወጥተው ወደ ሌላ የሰውነት ክፍል ከገቡ በሽታ ያስከትላሉ ። እነርሱም ከዓይነ ምድር ጋር ከወጡ በኋላ በሽንት መሽኛ ቧንቧ ይገባሉ ። ከዚያም በተለያየ ምክንያት ሽንት በፊኛ ውስጥ ከተጠራቀመ ተመልሶ ወደላይ የመገፋት ጠባይ ስላለው ባክቴሪያዎች በቀላሉ ወደ ኩላሊት በመግባት ይበክሉታል ።

በብዛት የሚያጠቃውም ሴት ሕፃናትንና ነፍሰጡር ሴቶችን ነው የሚያሳያቸው ምልክቶች በሚሸናበት ጊዜ የማቃጠል ስሜት ይሰማል ቶሎ ቶሎ ያሸናል ሽንቱም ደም የሚመስል ይሆናል ። በፊኛ አካባቢም ሕመም ይሰማል ።

ጠጠሩም ሊፈጠር የሚችለው በተለያዩ በሽታዎች ምክንያት ዕረፍት በማብዛት / ባለመንቀሳቀስ / በድርቀት እንዲሁም በሽንት መጠራቀም ነው ። በ

ወደ ገፅ ፰ ዞሯል



# «ኢየሱስን እንፈልጋለን»

ወቅቱ ፋሲካ ነበር አይሁድ በባህላቸው ፋሲካን ከምድረ ግብፅ ባርነት በወጡበት ጊዜ የበግ ጠቦት አርደው ግብፃውያንን የመታው መቅሰፍት ወደ እነርሱ ቤት እንዳይገባ የበራቸውን ጎበንና ፣ መቃን የቀቡበትን ቀን በማስታወስ በየዓመቱ የፋሲካን በዓል ያከብሩ ነበር ። ይህ ንንም በዓል በቤተ መቅደስ ሲያደርጉ የሚታረደው የበግ ደም የሚፈሰው በቄድሮን ወንዝ አካባቢ ነው ።

በዚህ በቄድሮን ወንዝ ደሙ ስለሚፈስ ይህ ወንዝ በደም የተቀላቀለ ስለሆነ ለፋሲካም የታረደውን የበግ ደም ጠራርጎ ይዞ የሚሄድ ወንዝ ነበር ። የአይሁድን ታሪክ ስንመለከት አንዳንድ ጊዜ አይሁድ ከሁለት እስከ አምስት ሺ. የሚደርስ በግ ያርዱ እንደነበር ታሪክ ያብራራልናል ። በዚህም አንፃር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የፋሲካውን ራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከበላ በኋላ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ የመጣ የእግዚአብሔር በግ እንደሆነና ስለ ዓለምም መስዋዕት ሆኖ የሚቀርብ መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ ገለጸላቸው ። በዚህ ጊዜ ይሁዳ አብሮ ነበር ።

ነገር ግን ይሁዳ አብሮ ከበላና የክርስቶስን ቅዱስ ቃል ከሰማ በኋላ ክርስቶስን ለመሸጥና ለማስያዝ ወደሚፈልጉት ሰዎች ዘንድ ሄደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይሁዳ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ቀድም ብሎ ያውቅ ስለረነበር ለጸሎት ወደ ጌቴሴማኒ ሄደ ።ጌቴሴማኒ የቄድሮንን ወንዝ ተሻግሮ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ያላች ትንሽ የአትክልት ስፍራ ናት ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህ ሁሉ በግ ደም እንደ ጎርፍ የሚወርድበትን የቄድሮንን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ጌቴሴማኒ ለጸሎት መሄዱን ስናስብ የቄድሮን ወንዝ ውኃ የከተማውን ቆሻሻ አጥቦ ከሚያፀዳው ይልቅ እውነተኛ የበጎች እረኛ የሆነው ክርስቶስ በደሙ የዓለምን ኃጢአት አጥቦ እንደሚያነጻው ያስገነዝባል ።

ይህም ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ በየጊዜው የሚፈሰው የዚህ ሁሉ በግ ደም ሰዎችን ከኃጢአት እንደማያነጻ ነገር ግን የእግዚአብሔር በግ ከሆነው ከሱ ደም በቀር ሰዎች ከኃጢአት እንደማይነጹ ያውቅ ነበር ። በተጨማሪም የመጣበት አላማ ይህ ስለነበር ወደ ጌቴሴማኒ ሄዶ ጸለየ ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ ደቀ መዝሙሩ የነበረው ይሁዳ ብዙ ጭፍሮችንና የጭፍሮቹን አለቆች እየመራ ኢየሱስን ፈልጎ ሊያሲዝና ለሞት አሳልፎ ሊሰጥ መጣ ።

ጊዜው ሌሊት ነበር ጌታችን ኢየሱስክርስቶስም የነበረው በጌቴሴማኒ ጫካ ስለነበር ችቦ ፋና ይዘው ተሰብስበው መጡ ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚሉት አንድ ጭፍራ የሚይዘው የጦር ብዛት በአይሁድ አቆጣጠር ስድስት ሺ. ሲሆን በሮማውያን ደግሞ ስድስት መቶ ነው ይህም አቆጣጠር በዚያ ዘመን የነበረ ነው ይህን ያህል ጦር የያዘ ጭፍራ ችቦና ፋና ይዞ ጋሻና ጦሩን አንግቦ አንድ ሰው ለመያዝ በሚመጣበትጊዜ በጣም እንደሚያስፈራ ለማንም የተሰወረ አይሆንም ። በተለይ የፋሲካ በዓል የሚከበርበት ጊዜ በመሆኑ የበዓሉን ሥነ ሥርዓት ያስከብሩ የነበሩት ጭፍሮች ሁሉ ከሊቀካህናቱ ከቀያፋ ከጸሐፍት ፈሪሳውያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘው እንዲያመጡ በተነገራቸው ጊዜ ፋና ፣ ችቦና መብራት እያበሩ ጦርና ፡ ጋሻ ይዘው ወደሱ ተረቡ ቢመለከትም ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቶ ዓለምን ለማዳን የመጣበት አላማ ስለሆነ ከሚጸልይበት ሥፍራ ወጥቶ ማንን ትፈልጋላችሁ አላቸው እነሱም የናዝሬቱን ኢየሱስን እንፈልጋለን አሉት » እሱም «እኔ ነኝ የምትፈልጉኝ እኔን ከሆነ አለሁላችሁ እነሱን ተዋቸው ይሂዱ » አለ። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ቁ ! - 8

ይህም አነጋገር የሚያሳየን በሱ ምክንያት አንድ ሰው ተይዞ መሞት ይቅርና መጉላላት እንኳን የማያስፈልገው መሆኑን ነው ምክንያቱም የሞትን ጽዋ ተቀብሎ ዓለምን ለማዳን የመጣበት ዋና ዓላማ ስለሆነ መከራውንም ፡ የሞትንም ጽዋ ቢሆን ሌላው ሰው እንዲካፈለው አልፈለገም « ከተሰጡኝ በጎች አንዱን እንኳ አላጠፋሁም»ያለው ቃል እንዲፈጸም የሞቱንም ጽዋ እራሱ ይጠጣዋል እንጂ ሌላ ሰው እንደማይካፈለው ስለሚያውቅ እኔን የምትፈልጉ ከሆነ እኔ እነሆኝ እነዚህን ግን ተዋቸው ይሂዱ ያለው ስለዚህ ነው ።

እኔ ነኝ የሚለው ቃል የሥልጣንና የኃይል አነጋገር መሆኑን ልንረዳ እንችላለን እርግጥም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊና አሸናፊ ነው ። የእግዚአብሔር የኃይል ስሙ እኔ ነኝ የሚለው ነው ። ከዘመናት በፊት ፡ ከሱም በፊት ማንም የለም ከዘመናትም በኋላ ማንም የለምና ይህንንም ልንረዳ የምንችለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ስምና ኃይል በሚናገርበት ጊዜ ሁሉም እየተተፈነገሉ ወደ ምድር ወደቁ በእጃቸውም የያዙት ፋናውም ፡ ችቦውም ፡ ጋሻውም ጦሩም ሰይፉም አንድ ላይ ወደቁ ።

በዚህ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቢፈልግ ኖሮ እነሱ ሲወድቁ ትቶአቸ ሊሄድ ይችል ነበር ይሁን እንጂ ይህች ሰዓትና ጊዜ ለሰው ልጅች ሕይወት አልፎ የሚሰጥባት ትክክለኛ ሰዓት ስለነበረች ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ሥፍራ መሄድ አልፈለገም ይህም ሌሎቹን ለማዳን እራሱ ለመሞት መምጣቱን ያመለክታል በዮሐንስ ወንጌልበምዕራፍ10 ከቁጥር ! - !2 « መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ስለ በጎቹ ነፍሱን አሳልፎ ይሰጣል ። ቅጥረኛ ግን ተኩላና ሌባ ቢመጣ በጎቹን ትቶ ይሸሻል » በማለት ራሱ መድኃኒታችን ተናግሮአል በሀገራችን ያለውን የእረኝነት ሥራ ስንመለከት እረኛው በጎቹን ወደፊት አስቀድሞ ከኋላ ይነዳቸዋል አውሬ ቢመጣ በመጀመሪያ የሚጋፈጡት በጎቹ ናቸው። በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የነበሩት የበጎች እረኞችን ታሪክ የተመለከ



www.ethiopianorthodox.org

ትን እንደሆነ ደግሞ በተለይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በነበረበት ወቅት እረኛ የሚሄደው ከበጎቹ ፊት ነበር ከዚያ በኋላ በጎቹ ይከተሉታል ። ገደልም ቢኖር ወንዙን ተሻግሮ እረኛው ለበጎቹ መስመርን ማሳየት ነበረበት በዚህ ጊዜ ነው መልካም እረኛ ነፍሱን ስለሌሎች ይሰጣል ተብሎ የተጻፈ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እውነተኛ እረኛ በመሆኑ ስለበጎቹ ተመታ ፡ ተንጋላታ ፡ ተገረፈ እስከ መስቀልም ሞት ድረስ ራሱን አሳልፎ ሰጠ መራራ የሆነውንም የሞት ጽዋ ቀመሰ በሌላበኩል ደግሞ እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈትነው እንደፈለገ እንመለከታለን « የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ማሪያም ሂድ ፡ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለው አብርሃምም በማለዳ ተነስቶ ልጁን ይስሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ እሳቱንና቎ቢላዋውን በእጁ እሱ ያዘው ሦስት ቀን ከተጓዙ በኋላ ከተራራው ደረሱ ።

አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ እንጨቱ ንም ረበረበ ልጁን ይስሐቅንም አሥሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው አብርሃምም እጁን ዘረጋ ልጁንም ይሠዋ ዘንድ ቢላዋ አነሣ የእግዚአብሄር መልአክም ከሰማይ ጠራና በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት አንድ ልጅህንም ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ » ዘፍጥረት 22 ከቁጥር 1 - 14

ይህ ታሪክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራንዮ ተራራ ላይ ስለሰዎች ኃጢአት መስዋዕት ሆኖ መቅረቡን ያሳስበናል ይኸውም እግዚአብሔር አብ ዓለሙን በሙሉ ስለወደደ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ አንድ ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት ማድረጉን ይገልጽልናል ።አርብሃም ልጁ ይስሐቅንለመስዋዕት የሚሆን እንጨት አሸክሞ ወደ መሰዊያው ቦታ ሲያመራና ሊሰዋው ሲወስደው እንዳልራራለት ሁሉ የሰማዩ አባታችንም አንድ ልጁን ስለ እኛ ኃጢአት መስዋዕት ሆኖ እንዲሰዋና መስቀል ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ተራራ ሲጓዝ አልራራለትም በዚህ ረገድ ይስሐቅ ስለ እሱ የሚሠዋ በግ ሲያገኝ በደል ያልሰራው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እኛ በጽድቅ እንድንኖር ስለኛ ኃጢአት በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ሞተ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና ።

እንግዲህ አይሁድ ኢየሱስን የፈለጉት ለመዳን ሳይሆን ሊሰቅሉት ፣ ሊገድሉት መሆኑን ተመልክተናል እኛስ ኢየሱስን የምንፈልገው ሕይወት ጤንነት ፡ መዳን እንዲሰጠን ነውን ? እንደ ጲላጦስ ፍርድእያጎደልን ከደሙ ንጹህ ነኝእያልን እጃችንን በውኃ መታጠብ ከሆነ ከሰቀሉት ከአይሁድ በምንም አንሻልም።

ሄሮድስም ክርስቶስን ይናፍቀውና ከብዙ ቀንም ጀምሮ ሊያየው ይፈልገው ነበር በመከራ ላይ ባየው ጊዜ ግን ጠላው እኛም ወንድሞቻችን በመከራ ላይ ሲወድቁ እያየን የማንረዳቸውና የመከራቸው ተካፋይ ካልሆን ኢየሱስን እንፈልገዋለን ብንል ከነፍስ ገዳዩ ከሄሮድስ ጋር እንደተባበርን እንቆጥራለን ስለዚህ ሁሉን እየወደድን የተሰቀለውን ኢየሱስን እንፈልገው ። ።

አሲቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## የኩላሊት በሽታ

ከገፅ ፮ የዞረ

ሌላ በኩልም ኩላሊት በተለያዩ ምክንያቶች በሰውነታችን ውስጥ የሚገኙትን በትክክል እያጣራ ማስወጣት ካልቻለ የእነርሱ ክምችት ጠጠር ሊሆን ይችላል ። ጠጠሩም የሽንት ቧንቧውን በመዝጋት የሽንቱ መጠን አነስተኛ እንዲሆን ወይም ጭራሽ እንዳይሸና ያደርጋል ። ከውስጥ በመቀመጡም ሴሎቹን በመፈግፈግ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። አንዳንድ ጊዜም ደምና ንጭ ሴሎች ከሽንት ጋር ሊወጡ ይችላሉ ።

በኩላሊት ላይ ሊወጣ የሚችለው እበጥ (እባጭ ) የተለያየ ቢሆንም ከእነርሱ መካከል 75 በመቶ በተለያዩ የሰውነት ዋና ዋና ክፍሎች እንደ አንጎል ፡ ጉበት ፡ ሳንባና ረግሸርም አጥንቶች ላይ ሊሰራጭ የሚችለው ዓይነት ነው ። ይህም በብዛት የሚታየው በወንዶች ላይ ሲሆን ሲጋራ ማጨስ የበሽታው መንስኤ እንደሚሆን ይገመታል። እንደዚሁም ደግሞ በጥጥ ፣ በቆዳና በጎማ ፋብሪካዎች የሚሠሩ ሰዎችም በሽታው ሲያጠቃቸው ይታያል ። ይህ በሽታ ምንም ዓይነት የሕመም ስሜት የሌለው ደም የመሰለ ሽንት ያሸናል ። ከፍተኛ የሰውነት ክሳትና ድካም እንዲሁም የደም ማነስ ያስከትላል ።

የኩላሊት በሽታ የሰውነትን ክብደት መቀነስ ብቻ ሳይሆን ሊጨምርም ይችላል ይህም የሚሆነው በሰውነት ውስጥ የሚገኙትን ፈሳሽም ሆነ ሌላ ጠቃሚ ነገሮች በተስተካከለ ሁኔታ ስለማያጣሩ በአንዳንድ ቦታዎች ተከማችተው ስለሚያሳብጡ ነው ። በተጨማሪም የቆዳ መጨማደድን የትንፋሽ እጥረት ፡ የሆድ ቁርጠት ፣ የምላስ መድረቅ ፡ የውኃ ጥማትና የምግብ ፍላጎት መቀነስ ሊኖር ይችላል ።

በአጠቃላይ ኩላሊት ጤናማ ካልሆነ ሥራውን በሚገባ ሊያከናውን ስለማይችል አስፈላጊ ነገሮች ለመላው ሰውነት ሳይደረሱ የማያስፈልጉትም ሳይወጡ ስለሚቀሩ ይህንና የመሳሰለውን ችግር ሊያመጣ ይችላል ።

ነርስ ተማሪ የሺሐረግ ሥርጋዌ



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## የቅዱሳት መጻሕፍት ቅኔዎች መንገድ

1- ሠምና ወርቅ የቅኔ መንገድ

2- "ንሰሰርና ሠም ለበስ ውስጠ-ወይራ"

የተሠኙትን የቅኔ መንገዶች ባለፈው ቁጥር ፶፬ እትም አሳይተናል ።

3- ተከታዩ አጥፊና ጠፊ የቅኔ መንገድ

አስረጅ፦ "የያዕቆብ ቤት እሳት ፡
የዮሴፍ ቤት ነበልባል
የዔሣው ቤት ገለባ ይሆናል"
(ትንቢተ አብድዩ ቁጥር 18 )

"ቃሌን በአፍህ ውስጥ እሳት (እንደ እሳት )
ይህንም ሕዝብ እንደማገዶ እንጨት አደርጋለሁ "
(ኤር 5፡14 )

4 - ከይጠ ወይማጠ የቅኔ መንገድ

አስረጅ "የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት ለምት ፈልጉ ወዮላችሁ
ከአንበሳ ፊት ለማምለጥ ሲሸሽ እንደገና ድብ እንደሚያጋጥመውና ከድብ አምልጦ ወደቤት ይገባና እጁን በግድግዳ ላይ ሲያስደግፍ በእባብ እንደሚነደፍ ሰው ነው ።"
(አሞስ 5፡19 )

ይህንም መሠረት በማድረግ ከኢትዮጵያ የቅኔ ሊቃውንት መካከል አንዱ የተቀኙትን እንደሚከተለው እንመልከት

መወድስ ዘንድንቆ ማርቆስ

ለዘጐየ ሰብእ አምገጸ አንበሳ
ኮኖ ዕሁበ ሶበ ተከውላ ገዳም ረከቦ
ወእመ ውስተ ቤት ቦአ ተረክቦተ አርዌ በሀቦ ንብረተ ዝንቱሰ ይመስል ንብረተ አዳም በሲኦል እንዘቦ
እስከ መንግሌከ ትቀጽቦ
ሥሉጠ ልደት ክርስቶስ ወመሥዋዕተ አብ ዘዲቦ በልቦ፡
እምገዘኒ እስምየከ ምክንያተ ብዙኅ የብቦ
ዘመድ ጽሩየ ልብ እንበሌከ እስመ አልቦ
እመኒ ትሁብ ዕረፍተ ወሀብተ መከራ ትሁቦ
እምርእስየ ለርእስየ እስመ አንተ ትቀርቦ

አባላሽን የቅኔ መንገድ

አስረጅ -"በግራ እጃቸው መንትፈው ይዘው ይርባቸዋል በቀኝ እጃቸው ይጐርሳሉ ነገር ግን አይጠግቡም ፡ እያንዳንዱ የጓደኛውን ሥጋ ይበላል ኤፍሬም ምናሴን ምናሴም ኤፍሬምን ይበላዋል (ኢሳ 9፡20-21 )

የዚህንም ተመሳሳይ እንደገና በትንቢተ ሚክያስ 3፡3-4 መመልከት ይቻላል አጠቃላይ ትርጉሙ የበደና ተበዩን ሥርዓት የሚያመለክት ነው ። (ኢሳ 49 26)

6- የአባት ዕዳ ለልጅ የቅኔ መንገድ

አስረጅ፦ "አባቶች መራራ የሆነ ኮምጣጣ ፍሬ በበሉ ልጆቻቸውን አጠረሳቸው " ይላሉ ። (ሕዝ. 18-2 )

ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይበልጣል ፡ ራሱን መግዛት የሚችል ሰው የጠላቱን አገር በጦር ኃይል አስለቅቆ ከሚወስድ አገር ገዥ ይበልጣል ። (ምሳሌ 16 ፡ 32 )

8- ምጸት የቅኔ መንገድ

አንድ ሰው ሊፈጽመው የሚችለውን ነገር እንደማይፈጽም ወይም የማይፈጽመውን ነገር መፈጸም እንደሚችል አስመስሎ የማሾፍን የንግግር ፈሊጥ ይገልጣል ።

አስረጅ፦ በመጽሐፈ ኢዮብ 38፡1-19 እግዚአብሔር "ኢዮብን ስለአስደናቂ የሥነ ፍረት አኗኗር (ህላዌ )

ሲጠይቀው ቆይቶ በመጨረሻ ላይ ከቁጥር ፲፱ እስከ ፳፩ እንዲህ ይለዋል"ኢዮብ ሆይ የብርሃን መመላለሻው መንገድ የት ነው? የጨለማውስ ቤት ወዴት አለ? በዚያን ጊዜ ተወልደህ ነበርና የዕድሜህ ቁጥር ብዙ ስለሆነ በዕውነት አንተ ይህን ሁሉ ሳታውቅ አትቀርም " ይህ እንግዲህ የምፀት አነጋገር መሆኑ ነው።

በመዝሙር ዳዊት 2፡4 ያለውን ከዚህ ጋር በማገናዘብ ምፀት የቅኔ ዘይቤ ምን እንደሆነ መረዳት ይቻላል ።

9- ተሰብኦት የቅኔ መንገድ

ይህም ዓይነቱ የቅኔ መንገድ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ እንስሳት አራዊትና ሌሎችም ተንቀሳቃሽ ፍጥረቶች ወይም ከነጭራሱ ግዑዛን የሆኑ ሕይወት የሌላቸው ፍጥረቶች በሰው ቦታ እየገቡ የሚነገሩበት ጥበብ ነው ።

አስረጅ "የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደእኔ ይጮሃል " ዘፍጥ 4፡ 10 ።

"ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች " ባለም ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያመለክታል ።(መዝ 67፡ 31)

ይህ እንግዲህ ለማስረጃ ያህል ባጭሩ ተጠቀሰ እንጂ በሰው ቦታ ገብተው የሚነገሩ ብዙ ዕልፍ አዕላፍ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ይገኛሉ ። በመጽሐፈ መሣፍንት 9፡7-21 በርከት ያሉ ዕፀዋት በሰው ቋንቋ በሰው ቦታ ገብተው እንዴት እንደተነገሩ መመልከት ይቢቃል ።

ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ቅኔዎች መዝገብ ስለሆነ ለሥነ ጽሑፍ ዕድገትና ለአእምሮ መስፋት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ መመልከት ይገባል ።

ቁ መክብብ አጥናው

## የመከራ ሳምንት

ከገፅ ፲፩ የዞረ

ኪዳናት እንዲሁም ከሊቃውንት ስለክርስቶስ ሕማምና ሞት የሚናገሩትን መጻሕፍት በማንበብ በጾም ፣ በጸሎትና በስግደት ነው ። ብዙ ክርስቲያኖች ይህን የሕማማት ሳምንት የሚያሳልፉት ጥሬ ቆርጥመው ውሃ ጠጥተው የጨው ቂጣ በልተው በመሬት ላይ ተኝተው ነው ። የላመ የጣመ አይቀምሱም በአልጋና በምቾት አይተኙም ። ይህም ሕማምና ሞት የማይገባው አምላክ ስዎችን ከመውደዱ የተነሣ የተቀበለውን ፀዋትወ መከራ ለማስታወስ በየጊዜው ለሚነሣው ትውልድም ፍቅሩን ቸርነቱንና አዳኝነቱን ለማስተማርና ለመመስከር ነው ።

ራደ አስረስ



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፡ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፡ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ ዓም ድ አዘጋጅ

አዲስ አበባ

እኔ ዲያቆን ነኝ ዕድሜዬም 15 ዓመት ነው ፤ የትምህርት ደረጃዬም 9ኛ ነው ። ነገር ግን ይህንን ሥጋዊ ትምህርት ባለመፈለጌ ከዚህ በፊት ማዕርገ ዲቁናን ሳልቀበል ከ4ኛ ክፍል ወድቄ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ በ1970 ዓ.ም. ማዕርገ ዲቁና ተቀብየ በ1972 ዓ.ም. 9ኛ ክፍል ደገምኩኝ ።

ስለዚህ አሁን የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቱን በመድኃኔ ዓለም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት ቤት በመከታተል ላይ ነኝ

ነገር ግን አሁንም የቤተ ሰቦቹን ፈቃድ ለመፈጸም በመማር ላይ ነኝ ።

የእኔ ፍላጐት የቤተ ክህነትን ትምህርት ተምሬ ማዕርገ ምንኩስናን ከቅስና ጋር አያይዤ በድንግልናና በንጽሕና ተወስኜ በዚህ በተቀደሰ ተግባር ተወስኜ ጌታየንና የእርሱን ተከታዮች አክብሬ ለመኖር ነው ።

ስለዚህ ለዚህ የተቀደሰ ሀሳቤ ምን ትመክሩኛላችሁ ? ምንስ ይሻለኛል ?

ከዚህም ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ያልገባኝ ጥቅስ አለ ፤ ይኸውም "እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ ወዮላችሁ ። ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ ይላል ። ይህንን ሲል ምን ማለቱ ነው ? አብራሩልኝ ።

ዲያቆን ኀይለ ኢየሱስ ሰይፉ
መድኃኔ ዓለም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት ቤት
የፖ.ሣ.ቁ. 3623 አዲስ አበባ

ዲያቆን ኀይለ ኢየሱስ ሰይፉ ፡ የጻፍ ክልን ጥያቄ ደርሶን ተመልክተዋል ፤ 1ኛው ጥያቄህ ምንኩስናን የሚመለከት ነው ። በመሠረቱ በዲቁና ሥራ ተሰማርተህ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያ ንና ምእመናንን ማገልገልህ ተገቢና የሚደገፍም ነው ስለዚህም ትመሰገናለህ ።

ይሁን እንጂ በንጽሕናና በምንኩስና ተወስነህ ለማገልገል ማቀድህን ገልጸ ህልናል ። በምንኩስና ለመኖር መመኘትህ መልካም ቢሆንም ይህንን ምኞትህን ለመፈጸም ዕድሜህ አይፈቅድልህም ። ምክንያቱም አንተ ራስህ እንደገለጽከው ዕድሜህ 15 ዓመት በመሆኑ በ15 ዓመት ውስጥ የትኛውን መከተል እንዳለብህ ስለማታውቅና ለአካለ መጠንም ስለአላደረስክ ነው ።

አንተ አሁን ያለብህ የጀመርከውን ትምህርት እየተከታተልክ በትርፍ ጊዜህም መንፈሳዊውን ትምህርት በመከታተል ሁሉንም ማጥናት እንጂ ገና ወደፊት የሚደርሰውን ፈተና ለመቋቋም የፈተና ተረካቢ የሆነው አካልህ ፈተናውን ለመቋቋም ከጊዜው ሳይደርስ ለምንኩስና ማሰብህ ተገቢ አይደለምና በንጽሕና ሁነህ እስከ ጊዜው እግዚአብሔርን በማገልገል ትምህርትህን ተከታቶል ። የወላጆቹን ፈቃድ ለመፈጸም ያህል እማራለሁ ብለሃል ።

ትምህርት የኑሮ መሠረት ፣ የሀገር ፍቅር መስታወት ፣ የእውቀት ሁሉ ቁንጮ በመሆኑ ትምህርትህን የምትከታተለው የወላጆችህን ፈቃድ ለመፈጸም ያህል ብቻ መሆኑን በመግለጽህ ነገሩ አስገርሞኛል ። ምክንያቱም ከማንኛውም ዓላማ በፊት መቅደም ያለበት ትምህርት ሲሆን አንተ ግን ለሰው ፈቃድ ብለህ ብቻ የምትከታተለው መሆንህን መግለጽህ ትክክል አይደለህምና ነው

ስማህ ዲያቆን ኃይለ ኢየሱስ ፤ እግዚ. እግዚአብሄርም የሚፈልገው ካህን፡የተማረ ማስተማር የሚችል ፣ የእግዚአብሔርን ንጹህ ቃል በምዕመናን ልብ መዝራት የሚችል እንጂ በማንኛውም ነገር ያልሰለጠነና ያልተማረ ካህን የእግዚአብሔርን ቤት ማገልገል አይችልምና ለትምህርት ቅድሚያ በመስጠት ከሁሉ በፊት ትምህርትን ተከታተል ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወላጆቹን በመርዳት ፋንታ የወላጆቹን ፈቃድ ሽሮ በብህትውና ወይም በምንኩስና ምክንያት ወደገዳም ወይም ወደምንኩስና የሚገባ ሰው አድራጐቱ ትክክል ስለ አልሆነ በፍትሕ መንፈሳዊ እንዲህ ተብሎ ተከልክሎአል ። "እናት አባቱን የማይረዳ፡ በብህትውና ምክንያት ሊያገለግላቸው የማይፈቅድ የተለየ (የተገዘተ) ይሁን) ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 10 ቁ 349 ይላል ።

ስለዚህ አንተም ወላጆችህ ሳይፈቅዱልህ ከእነርሱ ሥር ሳትወጣና አካለ መጠን አድርሰህም መብትህን ሳታከብር በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ሕግ ከ18 ዓመት በታች ያለ ልጅ በወላጆቹ ሥር የሚቸዳደር ስለሆነ ከእነርሱ ፈቃድ ውጭ እመነኩሳለሁ ብትል ሕግ አፍራሽ እንጂ ሕግ ፈጻሚ አይደለህምና ለምንኩስና የሚያበቁትን ነጥቦች እስከታሟላ በዲቁናው ሥራ እግዚአብሔርን እና ምዕመናንን እያገለገልህ መንፈሳዊውንም ሆነ ሥጋዊውን ትምህርትህን በመከታተል የአመክሮውን ጊዜ መፈጸም አለብህ ።



እኛም የምንሰጥህ ምክር ይኸው ነው ከዚህ በበለጠ ለመረዳት ብትፈልግ ግን በአካባቢህ የሚገኙትን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እየጠየቅህ ስለሕገ ምንኩስና መማርና መረዳት አለብህ ። በ2ኛው እንዲብራራልህ ስለጠየቅከው የወንጌል ጥቅስ ሶስቱ ወንጌላውያን ብዙ ባለ ተለያየ ሁኔታ እንደሚከተለው አብራርተውታል ። አብዝተን እንጸልያለን በማለት ምክንያት የድሆችን ገንዘብ የምትበሉዋቸው ወዮላችሁ ፤ በማለት የጸሎት ማብዛትን ጉዳይም ሲያትት ፡ አብዝተን እንጸልያለን እያሉ አብዝተው ሲጸልዩ በተለይ መብአውን የሚያቀርቡት ሴቶች ባሎቻቸው የሞቱባቸው መበለቶች ከሆኑ የባሎቻችንን ነፍስ ያስምሩልናል ፤ ልጆቻችንን ያሳድጉልናል እያሉ ለስጦታ ካዘጋጁትና ካሰቡት የበለጠ ወጭ አድርገው ይሰጡዋቸዋል ።

ስለዚህም ፈሪሳውያን እውነተኛውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበውን ጸሎት በመተው ጸሎትን የጥቅም መሰብሰቢያ ፤ የሰዎች ማታለያ ስለአደረጉት እንዲህ ዓይነቱን ጸሎት የሚያቀርቡት ፈሪሳውያን የመበለቶችን ቤት ለማሟጠጥና ለመተናኮል የሚያስረዝሙት ጸሎት ስለሆነ ጌታ እንዲህ ዓይነቶቹ ፈሪሳውያን የባሰ ፍርድ እንደሚደርስባቸው አስጠንቅቆአል ። ማቴ. 23 ፤ 13 ፤ ማር 12 ፤ 40 ሉቃ 11፤52

## የመከራ ሳምንት

ከገጽ ፫ የዞረ

መንፈቀ ሌሊት ድረስ በአካለ ሥጋ ስኩብ በመቃብር ሲሆን በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በግዞት ለነበሩ ነፍሳት ነፃነትን ሰበከላቸው ። 1ኛ ጴጥሮስ ፤፥18 በክርስቶስ ሕማመ ሥጋ የአዳምና የልጆቹ ሕማመ ነፍስ ተወገደ በክርስቶስ ኀጥእ መባል የአዳም በደል ተሠረየ ። ክርስቶስ መከራ መስቀልን በመሸከሙ በአዳም ልጆች ትከሻ ላይ የነበረው ከባድ የኃጢት ሸክም ከአዳምና ከልጆቹ ትከሻ ወረደላቸው ። በክርስቶስ ሞተ ሥጋ አዳም ከነልጆቹ ሕይወተ ነፍስን አገኘ ። መለኮት በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር በመውረዱ አዳም ከነልጆቹ ከሲኦል ወጣ ።

አዳምና ልጆቹ በሲኦል እንደ ተጣሉ ዩቀሩ ዘንድ እግዚአብሔር አልፈቀደም በሰይጣን ቁራኝነትም እንዳሉ ዩኖሩ ዘንድ አልተዋቸውም ከተጣኑበት ሊያሥነሣቸው ከቁራኝነት ነፃ ሊያደርጋቸው ወደደ እንጂ ይህንንም ሲያደርግ በአምላክነቱ ድል አልነሣውም ፤ በከሃሊነቱም አልተዋጋውም ። አልሠለጠነበትምም ከጌትነቱ ወገን በምንም በምን ድል አልነሣውም በልዩ ትሕትና በሠራው ሥራ ነው እንጂ ማለት ራሱን በትሕትና ዝቅ አድርጎ ትሑት ባሕርየ ሰብእን ተዋሕዶ በተዋሐደው ሥጋ ተገፍፎ ተገርፎ ተሰቅሎ በመሞቱ የሞትን ሥልጣን አጠፋ ስለዚህም እግዚአብሔር ዓለሙን ከፈጠረበት ጥበቡ ዓለሙን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል በማለት መጻሕፍት ይናገራሉ መምህራንም ያስረዳሉ ። (መቅ. ወን)

«...በግድ ያይደለ በፈቃዱ ከእኛ በነሣው ሥጋ ታመመ ፡ ተራበ ፡ ተጠማ ፤ መንገድ በመሄድ ደከመ ፡ በጥፊ ተመታ ፡ ተገረፈ ፤ ደኅንነትን በሚያድል በደሙ በከበረ መስቀል ላይ እጁን እግሩን ተቸነከረ ፡ ሕማም ሞት የሌለበት እርሱ እግዚአብሔር ቃል በሚታመምና በሚሞት ሥጋ ታመመ ።...» ለመራራ ሞት ከመገዛት ነፃ ስለ አደረገን ከጠላቶቻችን ከሰይጣንና ከሞት እጅ ስለ አዳነን በእግዚአብሔር እንመካለን በእውነት ሰው የሆነ እርሱ በእውነት ታመመ እንጂ በሐሰት አይደለም» (ሃይ አበ ዮሐ. ም. 114 ክፍ. 3፡25 ፡

"ራሱን አሳልፎ ለመስቀል ሰጠ እጁን እግሩን ተቸነከረ ጐኑን በጦር ተወጋ ከእርሱም ቅዱስ ምሥጢር የተገለጠበት ደምና ውሃ ፈሰሰ" (ሃይ አበ ባስልዮስ ም. 34 ክፍ. 5፡14 ። "እንዴት ታመመ ምሥጢሩን ግን ከላከው ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስም ጋር እርሱ ብቻ ያውቃል ፡ ይህንን ነገር መርምሮ ያውቅ ዘንድ ይረዳውም ዘንድ የ ሚቻለው ልቡና የለም ። (አባ አግሐፀን ነፍስየ) ብሎ ነፍሱን ከሥጋው ለየ በዓለመ ሥጋ በዓለመ ነፍስ ያሉትን ያድን ዘንድ የሞትን ሥልጣን የሚያጠፋ መለኮት በሥጋ ሞተ ... ምሥጢሩን የሚያውቅ ማንም ሳይኖር ያድነን ዘንድ ያደረገውን እርሱ ያውቃል ።) (ዮሐ. አፈወርቅ ም. 62 ክፍ. 1 ፡ 7 - 8)

አንድ አካል በመሆን ከሥጋ ጋር አንደሆነ እግዚአብሔር ቃል አንድ አካል ሆኖ በከበረ ሥጋው ደኅንነትን የተመላ ሕማምን ተቀበለ በመለኮት ሕማም የሌለበት ሲሆን ሰው እንደመሆኑ ዕዳ የሌለበትን ሕማም በሥጋ ታመመ ፡ ይኸውም መራብ ፡ መጠማት መንገድ በመሄድ መድከም ኃዘንና ትካዜ የሾህ አክሊል መቀዳጀት በፊቱ ምራቅን መቀበል በሎሌ እጅ በጥፊ መመታት በከበሩ እጆቹና እግሮቹ የተቸነከሩ ቅንዋት ተጠማሁ ባለ ጊዜ በመስቀል ላይ የጠጣው መጣጣ እኛን ለማዳን በከበረ መስቀል ላይ በሥጋው የተቀበለው ሞት ነው ። አንድ አካል በመሆን ከእርሱ ጋር አንድ በሆነ በሥጋ ሥርዓት እግዚአብሔር ቃል ይህን ሁሉ ተቀበለ፡ (ሃይ አበ ቴዎዶስዮስ ክፍል 2፡21)

የክርስቶስ ሕማምና ሞት ለዓለም ሁሉ ሕይወትን አስገኝቶአል ስለዚህም የሕማምትን ሳምንት በክርስቶስ ደም የተዋጁ ክርስቲያኖች ሁሉ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ያከብሩታል ። ሳምንቱ የሚከበረው ከብሉይና ከሐዲስ

ወደ ገጽ ፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## "በዚያ ጻድቅ ሰው ላይ ክፉ እንዳታደርግ»

ለባሕርዩ ጽድቅ እንጂ ኃጢአት ለሙነት እንጂ ሐሰት የማይስማማው መድኃኒታችንና አምላካችን ብቻ ነው እርሱ እውነተኛና ጻድቅ አምላክ ነው ፤ ሰዎች እምነትንና ምግባርን በአንድነት ይዘው ቢገኙ የጽድቅ ተካፋይ ይሆናሉ ፤ እምነት እያላቸው ምግባር ባይኖራቸው ግን ከጽድቅ ውጭ ናቸው ።

«በዚያ ጻድቅ ሰው ላይ ክፉ እንዳታደርግ» የተባለ ማን ፤ ስለምን መቼ? እንደሆነና «አታድርግ» የሚለውም ማን እንደሆነ ለመረዳት የማቴ.ወንጌል ፳፯፡፲፱ መመልከት ይጠቅማል ።

የተናገረችው አብሮቅላ የምትባል ሴት ስትሆን የተነገረለትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። የተነገረበት ጊዜ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ቢታው ኢየሱስ በአይሁድ እጅ ተይዞ ለፍርድ ከጲላጦስ ፊት እንደቆመ ጲላጦስም ባደባባይ ተቀምጦ ነገር ሲሰማ በነበረበት ወቅት ነው ።

ነገሩ እንዲህ ነው የጲላጦስ ሚስት የሆነችው አብሮቅላ ለባሏ በጻፈችው ደብዳቤ ላይ ስትገልጽ «በዚህ በጻድቅ ሰው ምንም እንዳታደርግ በዚህች ሌሊት በእርሱ ምክንያት በሕልሜ ብዙ ሥቃይ ሳይ አድሬአለሁ በማለት ትልክለች ያየችውም ሕልም ጲላጦስን ዘንዶ ሲውጠው እርሷን በእሳት አለንጋ ሲገርፋት አይታለች ስለዚህም ይህንን ያየችውን ባሏ በውሸት ምስክሮችና በነገር አሳማሪዎች እንዳይሳሳት በማሰብ ወደ ባሏ ደብዳቤውን ልካለታለች ። ያ ክፉ ጊዜ ብዙ ሰዎችን እንዳስተባበበ ወንጌሉን ሲነበበ አዲስ እያዘጋጀበትም ኢየሱስ በአይሁድ እጅ እንደተያዘ ሲበረውት የነበሩት ብዙ ተአምራት ሲያደርግ ያዩት ይወዱትና ያከብሩት የነበሩት እርሱም ይወዳቸው የነበረው ደቀ [illegible] ጥለውት [illegible] አብሮቅላ ግን ከዚያ ሁሉ ሰው በራእይ ስለታየችላት ለራሷ አምናው ባሏም እንዳይሳሳት አስጠንቅቃዋለች ይህ ራሱ ታላቅ ምስክርነት ነው ።

በእውነት ከተነጋገርን ሴቶች ለሚያምኑበት ነገር ወደኋላ እንደማይሉና አቅም እንኳን ቢያንሳቸው መላ አዋቂዎች እንደመሆናቸው መጠን በሥላቸው እንደሚጠቀሙ ከታሪክ እንረዳለን በአሁኑም አብሮቅላ ምስክር ልትሆን ትችላለች ። ብዙዎች ሴቶች ባሎቻቸውን ከመጥፎ ነገር በብልሃታቸው አድነዋቸዋል ። አብሮቅላም ባሏ እንዳይሳሳትና ፍርድ እንዳያጓድል ብዙ እንደጣረች እንገነዘባለን ።

በዘመነ ኦሪት የነበሩ ሴቶችም እንደዚሁ ብልሆች እንደነበሩ መጻሕፍት ይገልጻሉ ። ለምሳሌ ያህል አቢግያን የወሰድን እንደሆን ባሏ ናባል ሰነፍ እንደነበር መጽሐፉ ይገልጻል ይህም ዳዊት በሰላም የጠየቀውን በቁጣ መልሶ ዳዊትን እንዳስቆጣና ዳዊትም ሌላ እርምጃ ሊወስድ ሲል ብልኋ ሴት ሰነፉ ባሏ ሳይሰማ የሚፈልገውን በሙሉ አሟልታ ለዳዊት ስላቀረበች ባሏን ከሞት እንዳዳነችው እንረዳለን ። ይህ እንግዲህ ሴቶች ለሚመጣው ድንገተኛ ነገር ሁሉ ቶሎ ዘዴ ማግኘትና ቁጣንም ማብረድ እንደሚችሉና በተለይ ባሎቻቸውን በብልሀነታቸው ከሞት እንደሚያድኗቸው ያስረዳናል ።

ሌላዋ ጥበበኛ ሴት ደግሞ ያደረገችውን እንንገራችሁ ። በድሮ ጊዜ ነው አንድ አስተዳዳሪ የሀገሪቱን ሊቃውንት ሰብስቦ አንድ ጥያቄ አቀረበላቸው ። ጥያቄው እንዲህ የሚል ነበር ይህ እግዚአብሔር የምትሉት እሁድ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ሰኞ ከዚህ እስከ ብሩህ ሰማይ መልቶ የነበረው በየሥፍራው አዘጋጀ ማክሰኞ (አትክልትንና አዝርእትን ፤ ረቡዕ ፀሐይንና ጨረቃን ከዋክብትን ሐሙስ እንስሳትንና አራዊትን በሰማይ የሚበሩ አእዋፍን ፈጠረ ዓርብ ሰውን ፈጠረ ቅዳሜ ከሥራው አረፈ ትላላችሁ ይህ እግዚአብሔር አሁንስ ምን ይሠራል ብሎ ጠየቃቸው ሊቃውንቱም ምንም ሊመልሱለት አልቻሉም የዚህን መልስ ይዘን እንድንመጣ ቀጠሮ ይስጠን ብለው ጠየቁ ይባላል ። አስተዳዳሪውም ቀጠሮ ከሦስት ቀን በኋላ ሊቀርቡ ሰጣቸውና ከዚህ ከወጡ በኋላ እንግዲህ ምን እናድርግ ብለው ሲመካከሩ የዚህን መልስ ለማግኘት እግዚአብሔር በጥበቡ እንዲገልጽልን ከምግብ ተከለክለን ሱባኤ እንግባ ከዚያ የገለጸልንን እንናገራለን ተባብለው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ ። ከሊቃውንቱ መካከል አንደኛው ሊቅ ቤታቸው ሲገቡ ባለቤታቸው ምሳ አዘጋጅተው ኑሮ ምሳ ያቀርቡና እንብላ ይሏቸዋል እርሳቸውም አልበላም ይላሉ ሚስት ለምን አይበሉም ቢሏቸው የዋሉበትን የነገሩን ዝርዝር ሁኔታ ይነግሯቸዋል ። ሚስትም ነገሩን ያዳምጡና ታዲያ ለዚህ ጥያቄ ምን መልስ ሰጣችሁ ብለው ቢጠይቋቸው አልመለስንም ። ነገር ግን የዚህን መልስ እግዚአብሔር እንዲገልጽልን ሱባኤ እንድንገባ ስለተመካከርን ቀጠሮ ተቀብለን መጥተናል ። ስለዚህም ለ፫ ቀን ምግብ አንብላ ተባብለናል ይላሉ። ሚስትም ለዚህ ነው የማይበሉት አሁን ዝም ብለው ይብሉ መልሱን እኔ እነግረዎታለሁ ይሏቸዋል ። ባልየውም የሚስታቸውን እውቀትና ብልህነታቸውን ስለሚያውቁ ቃላቸውን አምነው ይበላሉ ። በእራት ጊዜም ንገሪኝ ቢሉ እነግረዎታለሁ እያሉ አስነበቷቸውና በቀጠሮው ቀን በይ አሁን ንገሪኝ ቢሏቸው መጀመሪያ ልብስዎን ይልበሱ ቁርስዎንም ይብሉ ብለው ሁሉንም ነገር ሲጨርሱ እንዲህ ይላሉ ሚስት እግዚአብሔር ከእሁድ እስከ ቅዳሚት ሰንበት ከላይ የተዘረዘሩትን ፈጥሯል ዛሬስ እግዚአብሔር ምን ይሰራል ለተባለው ጥያቄ መልሱ ግን ዛሬ እግዚአብሔር ቁና ይዞ በለውጥ ተራ ነው ያለው ይህም ማለት ፍትሐ ግፉአንን ሲመለከት ፍርድ ለጐደለው ሲያስተካክል በግፈኛ ሲፈርድ ለተገፋ ሲፈርድለት በጠቅላላው በፍርድ ማስተካከል ሥራ ላይ ነው የሚገኘው ለዚህም ማስረጃ የሚሆንህ ከአሁን በፊት አንተ ምን ነበርክ አሁንስ ከምን ደረጃ ላይ አለህ ካንተ በፊት የነበሩት እነ እገሌ ምን ነበሩ አሁንስ እንዴት አሉ እያሉ ሁሉንም በመዘርዘር አስረዷቸውና እንዲህ ብለው እንዲመልሱ ብለው ነገሯቸው ባልየውም ጥበበኛዋ ሚስታቸው የነገሯቸውን መልስ ይዘው በመሄድ ከጓደኞቻቸው ጋር ይገናኛሉ እህ ቢባባሉ ሁሉም ምንም የተገለፀልን ነገር የለም ይላሉ ።በዚህን ጊዜ እኚህ ሚስታቸው የነገሯቸው ሊቅ እኔ መልስ አለኝ ይላሉ እንግዳውስ እንሂድ ይባባሉና በቀጠሮአቸው መሠረት ወደ አስተዳዳሪው ይሄዳሉ አስተዳዳሪው ፊት ቀርበው በሉ መልሱን ንገሩኝ ይላል መልሱን ያገኙት ሊቅ ሚስታቸው እንደነገሯቸው አድርገው ሲናገሩ አስተዳዳሪው በመደሰት የተዘጋጀውን ሽልማት ሸለማቸው ይባላል ይህ አፈ ታሪክ ሳይሆን የቆየ እውነተኛ ታሪክ ነው ።

እንግዲህ እናስተውል ከላይ ሴቶች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉ ቶሎ መልስ ማግኘት የሚችሉ መላ አዋቂዎች ናቸው ላልነው ይህ ታሪክ ዋና ማስረጃ ሊሆነን ይችላል ። መጽሐፉ መልካም ሚስት ለባሏ አክሊል ናት ያለውም ትርጉሙ እዚህ ላይ ሊገኝ ይችላል እኒህ ሴት የባላቸው አክሊል ሆነው ባላቸውን ሊያሾሙና ሊያሸልሙ ችለዋል እነዚያ ሁሉ ሊቃውንት ሲያወጡ ሲያወርዱ ስንብተው ያላገኙትን መልስ እኒህ ሴት በደቂቃ ሊያገኙ ችለዋል ስለዚህም ሴቶች በተፈጥሮአቸው ምን ያህል ጥበበኞች እንደሆኑ ሲያስረዳን ዘመናዊ ጥበብ ሲጨምሩበት ደግሞ በእውቀታቸው የላቁ እንደሚሆኑ ያስረዳናል

ስለዚህም አብሮቅላ ባሏ ጲላጦስ በፍርድ እንዳይሳሳት እንደረዳችው ሁሉ እኒህም ሴት ባላቸው በህዝብ ፊት ሞገስን እንዲያገኙ ረድተዋል እኛም ዛሬ የነዚህ ፍሬ የሆነው ልጆቻቸው ቅሩትን ከኛ አርተን እንደ እናቶቻችን ጥበበኞች እንድንሆን ተግተን እንሥራ ።

# ደብዳቤዎች

ከገፅ ፩ የዞረ

ድሃም ይሁን ባለጸጋ በክርስቶስ ለአመነ ወንጌልን ለተቀበለና በዕውነት ወደ እርስዋ ለሚመጣ ሁሉ ነው እንጂ

ስለዚህም መልእክትዋ እንዲህ የሚል ነው ” ባለጸጋውን ስለባለ ጸጋነቱ አያፍረውም እንደ ተገመገመለት ነው እንጂ ፤ለድሃውም ስለ ድኅነቱ አይራራለትም እርሱን ደስ ካላሰኘው »አትናቴዎስ

ቅዳሴ ቁ. 77 ቤተ ክርስቲያን ድሆችንም ሆነ ባለጸጎችን በእኩልነት እየተቀበለች ታስተምራለች ታስተናግዳለች እንጂ አንተ ድሃ ነህ በድኅነትህ ብቻ ውጣ አንተ ባለጸጋ ነህ በባለጸግነትህ ብቻ ግባ አትልም እንዲያውም ባለጸጋው ድሃውን ኃይለኛው ደካማውን እንዲረዳው ትመክራለች ። ግን አንዳንድ ሰዎች በዕውነት ቤተ ክርስቲያንን ተሳልመው ቃለ እግዚአብሔር ሰምተው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ለመመለስ ሳይሆን ምእመናን ጫማቸውን አውልቀው በስተኋላቸው ሲያስቀምጡ ብድግ ለማድረግ እንደሚመጡ ንብረታቸው ከተወሰደባቸው ምእመናን ተረጋግጦአል እንዲህ አይነት ጠባይ ያላቸው ሰዎችም አንዳንድ ጊዜ አዳፋ ለብሰው ድሃ መስለው ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጥሩ ለብሰው ጨዋ ሰው መስለው ይገቡና በጫማ የመጣውን ሰው ያለጫማ እንዲመለስ ያደርጉታል ፤ በተለይ ሰው በዛ ባለበት ዓመት በዓል ቀንማ ጫማችን ተወሰደብን ከኪሳችን ገንዘብ ተዘረፍን የሚሉ ሰዎች ብዙ ናቸው ። ታዲያ የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪዎች በተቻለ መጠን የተሳለሚዎችን ገንዘብና ሕይወት ለመጠበቅ በግምት የሚጠረጥሩአቸውን ሰዎች ከዚህ ምን ታደርጋላችሁ? ብለው ቢጠይቁና የጠረጠሩትንም ሰው ወደ ውጭ ሁን ቢሉ ይመሰገናሉ እንጂ አይወቀሱም ፤ ሊወቀሱና ትምህርት ሊሰጣቸው የሚገባስ ክርስቲያን መስለው ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ ያላስተመጡትን የሚያየኑት ክፍሎች ነበሩ የሚሰሙበት ዕዝነ ልቡና የላቸውም እንጂ ።

ስለዚህ ጠያቂው ዲያቆን በላይ ጸጋዬ እንዲረዱት የሚያስፈልገው ቤተ ክርስቲያን በትክክለኛ እምነት የሚቀርቡትን ሁሉ ትቀበላለች እንጂ ደሃና ባለጸጋ አትልም ሥነ ሥርዓት ተቈጣጣሪዎችም የምእመናንን ደኅንነት ለመጠበቅና የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ሥርዓት ለማስከበር እንጂ ድሆችን ከባለጸጎች እየለዩ ለማስወጣት የቆሙ አለመሆናቸውን ነው ።





www.ethiopianorthodox.org


# ጸሎተ ሐሙስ

የፍቅር ጀማሪ የትሕትና መሥራች
የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ከሰማያዊ ዓለም ወደ ምድራዊ ዓ
ለም የመጣው እንዲሁ ያለ ም
ክንያት አልነበረም የመጀመሪያው ሰ
ው ሊሠራው የማይገባውን ኃጢአት በ
መሥራቱና እግዚአብሔርን በማሳዘኑ
እንደገና ከበደሉ ተመልሶና በሠራው
ኃጢአት ተጸጽቶ እያለቀሰ እግዚአብ
ሔርን ለመነ በተሰበረ ልቡናም የኃጢአ
ቱን ይቅርታ ጠየቀ በዚህም ወቅት እ
ግዚአብሔር አንድ የሚድንበትን ተስ
ፋ አሰማው የሰጠውም ቀጠሮ ከልጅ
ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ተሰቅየ አድ
ንሃለሁ የሚል ነበር ።

ይኸውም አዳም ከእግዚአብሄር ቀ
ጠሮ ተሰጥቶት እንደነበረ ሐዋርያ ቅ
ዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው
መልእክቱ ወአመ በጽሐ ዕድሜሁ ፈነ
ወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እ
ም ብእሲት እግዚአብሔር ለአዳም የሰ
ጠው ተስፋ በደረሰ ጊዜ ልጁን ላከ ከእ
መቤታችን ም ተወለደ ገላ .፬.፬ ሲል
አረጋግጧል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ
ሰጠው የደህንነት ተስፋ መሠረት ል
ክ በሰጠው ቀጠሮ መለኮታዊ ባሕርዩ
ን በሥጋ ሰውሮ የሰውን ባሕርይ ባሕ
ርይ አድርጎ ፍጹም አምላክ ሲሆን ፍጹ
ም ሰው ሆኖ ከእመቤታችን ከቅድስት
ድንግል ማርያም ተወለደ የማይታይ ረ
ቂቅ መለኮት ከግዙፍ ሥጋ ጋር ተዋሕዶ
ታየ ተዳሰሰ አምላክ ሰው ሆነ
ሰውም አምላክ ሆነ ። በዚህም
መሠረት ከኃጢአት በስተቀር
ሰው የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እየ
ሠራ በሥጋ የወለደችው ቅድስት ድን
ግል ማርያም ን እያገለገለ በግዕዘ ሕፃ
ናት ጥቂት በጥቂት አደጋ በዚህአይነት
አገልግሎት እያገለገለ33ዓመት ከ3ወርሰ.
ሆነው ወደዚህ ወደ ምድራዊ ዓለም የ

መጣው ዋና ዓላማው በሞቱ ለሰው ል
ጆች ሕይወትን ለማደል በእሱም ቁስል
በሰው ላይ የነበረውን ቁስለ ኃጢአት
ለመፈወስ ነውና ዓርብ ቀን ሊሰቀል
ና ራሱን መስዋዕት አድርጎ ሊያቀርብ
የዓርብ ዋዜማ ሐሙስ ውኃ በኩስኩስ
ት አቅርቦ የደቀ መዛሙርቱን እግር አ



ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ አዲስ ሥርዓተ ቁርባን እንደሠራ

ጠበ ። ሁሉም አንድ ሳይቀር በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ታጠቡ ይህም
ሕጽበት 1ኛ ትእምርተ ትሕትና ሲሆን
2ኛ ግን በዚሁ ዕለት ደቀ መዛሙርቱን
እንዳጠመቃቸው ያጠይቃል ። ጥምቀ
ት መሆኑም የሚታወቀው የደቀ መዛሙ
ርቱን ዕግር ሲያጥብ ከቆየ በኋላ ከጴጥሮ
ስ ሲደርስ ጴጥሮስ ትሕትና ያደረገ መ
ስሎት እኔ ባንተ እጅ አልታጠብም አ
ለው ግን ጌታ ጥምቀት መሆኑንሲያረ
ጋግጥለት እኔ ካለጠብኩህ ከእኔ ጋር ዕ
ድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የለህም ሲለው ክ
ርክሩን ትቶ እንግዲያስ እግሬን ብቻአይ
ደለም እግሬንም ራሴንም ነው እንጂ ብ
ሎታል እውነተኛ ጥምቀት ባይሆን ኑ
ሮ አልብከ ክፍል ምስሌየ ከእኔ ጋር

ክፍል የለህም ባላለውምነበር ሲሉ ኢ
ትዮጵያውያን ሊቃውንት ያትታሉ ።
ጌታችን ኢየሱሳ ክርስቶስ የደቀ መዛ
ሙርቱ ን እግር ካጠበ በኋላ ዝም አላለ
ም የሰው ልጅ የእሱን አርአያ እንዲከተ
ል ለማስረዳት “ እኔ ለእናንተ እንዳደ
ረግሁላችሁ እናንተም እንዲሁ ለሌሎ
ች ታደርጉ ዘንድ ምሳሌነትን ሰጥቻች
ኋለሁ” በማለት አስረድቷል ።

እንግዲህ ይህ በሰሙነ ሕማማት መ
ካከል የሚገኘው ሐሙስ ከሌሎች የሐ
ሙስ ቀኖች ተለይቶ ጸሎተ ሐሙስ የሚ
ል ቅጽል ሊያገኝ የቻለው በመስቀል ተ
ሰቅየ አድንሃለሁ ሲል የሰጠውን ተስፋ
ለመፈጸምና እንዲሁም ነቢዩ ኤርምያ
ስ እንሆ ከእሥራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤ
ት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወ
ራት ይመጣል” ትን.ኤር 31 :31 ።ሲል
የተናገረውን ትንቢት ለመፈጸም ሲሆን
እንዲሁም ማዳን የማይችለውን የላምና
የፍየል መሥዋዕት ሽሮ ራሱን አማናዊ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



# ጴጥሮስ በስቅለት ሌሊት

የሐዋርያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ
ስሙ ስምዖን ነበር ለሐዋርያነት ከተመ
ረጠ ወዲህ ግን ጴጥሮስ ተብሎ ተሠይሟ
ል ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በመጀመ
ርያ የተመረጠው እርሱ ነው ለሐዋርያ
ነት ከመመረጡ አስቀድሞ ሥራው ዓሣ
ማጥመድ ነበር የተመረጠውም ዓሣ ለማ
ጥመድ ከሄደበት ከገሊላ ባሕር ዳርቻ
ነው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕ
ለታት አንድ ቀን በሚያስተምርበት ጊ
ዜ ለደቀ መዛሙርቱ ሰዎች እኔን ማን
ይሉኛል የሚል ጥያቄን አቅርቦ ነበርጥ
ያቄውንም ያቀረበው ብርሃን መለኮቱን
ለደቀመዛሙርቱ ከመግለጹ አስቀድ
ሞስድስትቀን ሲቀረው የፊሊጶስ ከተማ
ተብላ በተሰየመችው ቂሣርያ ነበር ።

ክርስቶስ ላቀረበው ጥያቄ ከሰማዕያ
ኑ ብዙ መልሶች ተሰጥተዋል አንዳንድ
መጥምቁ ዮሐንስ ነው ይሉሃል ሲሉ
ሌሎች ደግሞ ኤልያስ ነው ፣ኤርምያስ
ነው ፡ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃ
ል ብለውታል ። ጌታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ለጥያቄው መልስ ከደቀ መዛሙ
ርቱ እንዲሰጠው ስለፈለገ ወደ ደቀመ
ዛሙርቱ መለስ ብሎ እናንተስ እኔ ማን
እንደሆንኩ ፣ትመሰክሩላችሁ አላቸው
በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ “አንተ የሕያው እግዚ
አብሔር የባህርይ ልጅ ክርስቶስ ነህ”
አለው ። ክርስቶስም መልሶ “የዮና ል
ጅ ስምዖንሆይ በሰማያትያለው አባቴ እን
ጂ ሥጋና ደም ይህንን አልገለጠልህም
ና ብፁዕ ነህ እኔም እልሃለሁ አንተ መሠ
ረት ነህ በአንተ መሠረትነት ቤተ ክር
ስቲያንን አሠራለሁ የገሃነም ደጆችም
አይችሏትም የመንግሥተ ሰማያትንም
መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ በምድር ያሠር
ከው ሁሉ በሰማያት የታሠረ ይሆናል
በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት
የተፈታ ይሆናል ።በማለት ሥልጣነ ክህ
ነትን እንደሚሰጠው አበሠረው ማቴ
16፡13-20

እንዲሁም ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌ
ም እንደሚሄድና በዚያም ከሽማግሌዎ
ች ፣ከካህናት ፣ከአለቆች ፣ከጸሐፎች
ብዙ መከራን ተቀብሎ እንደሚሞት
ሙቶም በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ
ናዓለምን እንደሚያድን ለደቀመዛሙር
ቱ ሲገልጥላቸው ሐዋርያው ጴጥሮስ
ጌታ ሆይ ይህ ባንተ ላይ ሊፈጸም አይ
ገባም በማለት የክርስቶስን ቃል
ማስተባበል ሲጀመር ክርስቶስ ጴ
ጥሮስን ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይ
ጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አ
ታስብምና ዕንቅፋት ሁነህብኛል በማ
ለት ገስጾታል ማቴ 16፡21 ከላይእንደ
ተጠቀሰው ክርስቶስ በቂሳርያ ከተማ
ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄን ካቀረ
በ ከስድስት ቀን በኋላ ብርሃን መለኮቱ
ን ለማሳየት ወደረጅምተራራ ይዟቸው
ከወጣ ሦስት ደቀመዛሙርት አንዱ ጴ
ጥሮስ ነበር ።

በተራራ ላይ የክርስቶስ ፊት ተለው
ጦ እንደ ፀሐይ ሲበራ ፣ ልብሱም እንደ
በረዶ ነጭ ሲሆን ሙሴና ኤልያስ ከእር
ሱ ጋር ሲነጋገሩ በዚያው ተራራ ላይ
ጌታ ሆይ በዚህ መኖር ለእኛ መልካም
ነውና በዚህ ሦስት ዳሶችን እንሥራ አን
ዱን ለአንተ ፣አንዱን ለሙሴ ፣አንዱን
ም ለኤልያስ የሚል አሳብ ያቀረበው
ሐዋርያው ጴጥሮስ ነው ፣እንዲሁም ክ
ርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ወ
ደ ቅፍርናሆም ከተማ በመጣ ጊዜ ግብር
የሚቀበሉ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ መጥተ
ው ጴጥሮስ ሆይ ለምን ይመስልሃል?
የምድር ነገሥታት ቀረጥና ግብር ከማን
ይቀበላሉ? ከልጆቻቸው ወይስ ከእንግ
ዶች ? አለው

ጴጥሮስም ከእንግዶች ነው ስላለው
ኢየሱስ እንግዲያስ ልጆቻቸው ነፃ ናቸ
ው ፣ነገር ግን እንዳናሰናክላቸው ወደ ባ
ሕር ሂደህ መቃጥንህን ጣል በመጀመሪ
ያ የሚያዘውን ዓሣ ውሰድና አፉን ስትከ
ፍት ሁለት እስታቴር ታገኛለህ እስታ
ቴር በኢትዮጵያ ሁለት ብር ነው ይላሉ
ያንን ወስደህ አንዱንስለእኔ አንዱንስለ
አንተ ስጣቸው ስላለው እንደታዘዘው
ግብሩን ገብሯል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም
መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብበት ጊዜሲቃ
ረብ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ በአይሁ
ድ እጅ ሲያዝ ሁላቸውም ጥለውት የሚ
በታተኑ መሆናቸውን ነገራቸው በዚህ
ጊዜ ጴጥሮስ ሁሉም ቢክዱህ እኔ በፍጹም
አልክድህም በማለት ተናገረ ፣ኢየሱስ
እውነት እልሀለሁ በዚያች ሌሊት ዶሮ
ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው
ጴጥሮስ ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚ
ያስፈልግ ቢሆን ከቶ አልክድህም ሲል
ደጋግሞ ተናግሮ ነበር ።

ክርስቶስ በአይሁድ እጅ በተያዘ ጊዜ
መላው ደቀ መዛሙርት ጥለውት በየፊናቸ
ው ሲበታተኑ ሐዋርያው ጴጥሮ በተ
ናገረው መሠረት በሩቅ ሆኖ እየተከተለ
እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ የነገሩን
ፍጻሜ ያይ ዘንድ ወደ ግቢው ገብቶ አለ
ባሌ መስሎ ክርስቶስን ለመግደል ከተ
ባበሩት ጋር አብሮ ተቀመጠ ።
ከዚያም ተቀምጦ ሳለ አንዲት ሴት ወደእ
ርሱ ቀርባአንተ ከገሊላውሰው ከኢየሱስ
ጋር ነበርህ አላቸው ጴጥሮስ ግን የም
ትይውን ኢየሱስን አላውቀውም ብሎ
ከዚያ በተሰበሰበው ሁሉ ፊት ካደ ።

ወደበሩም ሲወጣ ሌላይቱ ሴት አየች
ውና በዚያ ላሉት ይህ ሰው ደግሞ ከናዝ
ሬቱ ከኢየሱስ ጋር ነበረ አለች ዳግመኛ
ም ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ካደ ።

ጥቂት ቆይቶ በዚያው ከነበሩት ሰዎ
ች ቀረብ ብለው ጴጥሮስን አነጋገርህ ያ
ስታውቃልና አንተ በእውነት ከኢየሱ
ስ ተከታዎች ነህ አሉት በዚያን ጊዜ ጴ
ጥሮስ በዕርግጥ ያወቁኝ መስሎት በጣ
ም ይነገጠና አሁን የምትሉትን ኢየሱስ
ን አላውቀውም አለና የያዘውን እየጣለ
እንዲህ ይጣልኝ እያለ ካደ ወዲያውም
ዶሮ ጮኸ በዚህ ጊዜ ዶሮ ሳይጮህ ሦስ
ት ጊዜ ትክደኛለህ የሚለው ቃል ተፈ
ጸመ ።

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቲያናዊ ጋብቻ

ጋብቻ በፈቃደ እግዚአብሔር በጥንት ተፈጥሮ የተመሠረተ ቅዱስ ሕግ ነው ። ጋብቻ ለመረዳዳት ለመባዛት መልካም ዘርን ለመተካት ራስን በሕግ ወስኖ ለመያዝ ሁለት ፆታዎችን በፍቅር እንዲዋሐዱ የሚያደርግ የአንድነት ሥርዓት ነው ። በአንድነት ሆነውም ኑሮአቸውን ይመሠርታሉ ይገነባሉ ሁለቱም የኑሮን ቀንበር በጋራ ይሸከማሉ ። በዚህ ጊዜ ሴት ለወንድ የምትመች ረዳት ሆና መፈጠሯን ከእግዚአብሔር ቃል ልንረዳ እንችላለን ቃሉም እንዲህ ይላል "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት በማለት እግዚአብሔር አምላክ ሴትን ለወንድ ረዳት አድርጎ እንደሰጠው ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል ።(ዘፍ 2፡18 ) ስለዚህ ጋብቻ ከአምላክ የተሰጠ ቅዱስ ሥርዓት በመሆኑ በዘመነ ሥጋዌም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት ከደቀ መዛሙርቱና ከእናቱ ጋር ተገኝቶ ያከበረው የመጀመሪያ ተአምሩን የገለጸበት ባልና ሚስት የፍቅርና የፈቃድ ተዋህዶ የሚያደርጉበት ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ቋሚ ሕግ ነው ።
(ዮሐ.2፡1-12 ) ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ። (ማቴ. 19፡5-6 )

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት በተክሊልና በቅዱስ ቁርባን ዲያቆን ክፍሌ ደሳለኝና ወ ት ወርቅነሽ ብሥራት ጥቅምት 29 ቀን 74 ዓም በደብረ ብርሃን ጎሕ ቅ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጋብቻቸውን ፈጽመዋል ። ሥርዓተ ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊልና በቅዱስ ቁርባን ከፈጸሙ በኋላ የሦስቱም የሃይማኖተ አበው ቅ ማኅበራት የደ ብርሃን ቅ ሥላሴ ፣ የጎሕ ቅ ጊዮርጊስና የደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም መንፈሳውያን ወጣት መዘምራን በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው ሥርዓት በመገኘት ከዚያም ለቅዱስ ጋብቻ የሚገባውን መንፈሳዊ መዝሙር በመዘመር የቤተ ክርስቲያኑ ቀሳውስትና ዲያቆናት ልብሰ ተክህኖ እንደለበሱ መዘምራን ከህናትም "ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ" እያሉ ሙሽራውንና ሙሽራይቱን በደመቀ ሁኔታ አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።



ዲያቆን ክፍሌ ደሳለኝና ወ/ት ወርቅነሽ ብሥራት ሥርዓተ ጋብቻ በፈጸሙበት ወቅት

የሁለቱን ወጣቶች መንፈሳዊ አቋምና የአገልግሎት ታሪክ በአጭሩ ለመግለፅ ያህል ፡- ዲ ክፍሌ ደሳለኝ በጎሕ ቅ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለ14 ዓመታት በዲቁና ያገለገለና በማገልገል ላይ የሚገኝ ነው ። በተጨማሪም በደ ብርሃን ጎሕ ቅ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሚገኘው ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅርንጫፍ ማኅበር ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ለ5 ዓመታት በሊቀ መንበርነት ፣ ለ2 ዓመታት በዋና ጸሐፊነት አገልግሎአል ፣ በማገልገልም ላይ ይገኛል ። እንዲሁም የማኅበሩን መንፈሳውያን ወጣቶች በመመከል በቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ ለሁለት ዓመታት አገልግሏል ። የአካባቢው ወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበራት እንዲጠናከሩና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉ በተዋህዶ ሃይማኖታቸው እንዲፀኑ ከሚያበረታቱት የቤተ ክርስቲያናችንንም መሻሻል ከሚጠባበቁት መንፈሳዊ ቅንዓት ካላቸው ወጣቶች አንዱ በመሆኑ በመልካም ጠባይና ተግባሩ በአካባቢው ምእመናን ዘንድ የተወደደና የተመሰገነ መልካም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መንፈሳዊ ወጣት ነው ። ምእመናኑም ለዚሁ ወጣት ካላቸው ፍቅር የተነሣ የጋብቻቸው ሥነ ሥርዓት በአካባቢው ታይቶ የማይታወቅ ደማቅ በዓል ሆኖ ታይቷል ። የማይረሳ ትዝታም አሳድሮአል ። እንዲሁም ከላይ ስሙና መንፈሳዊ አገልግሎቱ የተጠቀሰለት የኑሮ ጓደኛ የሆነችው ወ ት ወርቅነሽ ብሥራት በምትኖርበት አካባቢ ተወዳጅ ጠባይ ያላት ሃይማኖቷን ወዳድ ጠባየ መልካም ወጣት ናት።ሁለቱ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት የፈጸሙት ቅዱስ ጋብቻ በአካባቢው ለሚገኙ ወጣቶች ጥሩ አርአያ እንደሚሆን እንጠራጠርም ። የፈጸሙት አድራጎት የሚያስደስት በመሆኑ በብዙዎች መንፈሳዊ ቅንዓትን አሳድሮአል ። ከላይ የተጠቀሱት ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ አገልጋዮች እንደሚሆኑ ያለፈው ሕይወታቸው ያስረዳል ፣ ወደፊትም በኑሮአቸው ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያከብሩና እንዲያስከብሩ የተቀደሰ ኑሮ እንዲሆንላቸው መንፈሳዊ ምኞት እንመኝላቸዋለን ።

ወልደ ቂርቆስ አበበ
የማኅበሩ ሊቀ መንበር



# «ሰባት ዓመት እንደ አንድ ቀን »

«በእግዚአብሔር ዘንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ይቆጠራል » የሚል በቅዱሳት መጻሕፍት አለ ። በዚህ አንፃር በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሥቃይና መከራ የተቀበለውን ቅ ጊዮርጊስን በማስታወስ ኢትዮጵያ ዊው ደራሲ ቅ ያሬድ ዝማሬ በተባለው ድርሰቱ የሰባት ዓመቱን ተጋድሎ ሲገልጽ «ሰባትዓመት ሙሉ የተሠቃየው ቅ ጊዮርጊስእንደአንድቀን አልመሰለውም » በማለት በአድናቆት ዘምሮለታል።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ትውልድ ሀገሩ ፋርስ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ወላጅ አባቱ አንስጣስዮስ ወይም « ዞሮንቶስ » እናቱ ቴዎብስታ ይባላሉ ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በተወለደበት ዘመን የኘን ሀገር የሚመራው ንጉሥ ዱድያኖስ ይባል ነበር የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት ዞሮንቶስ ከቤተ መንግሥቱ ሹመት ተሰጥቶት ሲሠራ ከቆየ በኋላ ጊዮርጊስ በተወለደ በ20 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ።

በወቅቱ አባት ሲሞት ልጅ ተተክቶ መሥራት የተለመደ ሕግ ስለነበር ። ቅዱስ ጊዮርጊስ የአባቱን ሥራ ለመጠየቅ ወደ ቤተ መንግሥት ሔደ ።
ከቤተ መንግሥቱም እንደደረሰ ዱድያኖስ የተባለው የሀገሩ መሪ ጣዖቱን ከፍ ባለ ቦታ አቁሞ ራሱ ለጣዖቱ ሲሰግድና ሕዝቡም ከእርሱ ጋር በመተባበር ሲሰግድ ሲወድቅና ሲነሣ አየ ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሁኔታው ስለአሣዘነው በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት ሳይፈራና ሳያፍር የክርስቶስ ተከታይ መሆኑን ገልጾ ንጉሡና ሕዝቡ የሚሰግዱለት ጣዖት ማዳን የማይችል ደካማ ፍጡር መሆኑን ከአስረዳ በኋላ ሰማይና ምድርን ለፈጠረ አምላክ እንዲሰግዱና እርሱን እንዲያመልኩ አስተማራቸው ዱድያኖስ ግን በፍቅረ ጣዖት የተመረዘ ስለሆነ የቅዱስ ጊዮርጊስን ትምህርት ሰምቶ ከአምልኮተ ጣዖት ተመልሶ በእግዚአብሔር ለማመን አልፈለገም ።

እንዲያውም ገድሉ እንደሚናገር እርሱ የሚሰግድለት ጣዖት ከእውነተኛው አምላክ እንደሚበልጥ በድፍረት ይናገር ጀመር ።

በተጨማሪ እርሱ ለሚያመልከው ጣዖት ቢሰግድ ከአባቱ የበለጠ ሹመትና ክብር እንደሚሰጠው ለቅዱስ ጊዮርጊስ ደጋግሞ ነገረው ። ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን የእግዚአብሔርን ኃያልነትና ከሃሊነት በሚገባ ያወቀና የተረዳ በመሆኑ የዱድያኖስን ቃል አልተቀበለም ጊዜያዊ ሹመት ሽልማት አልማረከውም ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በክርስቶስ ስም በሚመሰክርበት ጊዜ ልዩ ልዩ ተአምራት በማሳየቱ ያላመነውን ሕዝብ ወደ ክርስቶስ መልሷል ። ከሠራቸው ተአምራት አንዳንዶቹን አቅርበናቸዋል ።
፩ኛ በአንዲት መበለት ቤት ገብቶ የደረቀውን ምሰሶ ስላለመለመው የክርስቲያን አምላካቸው ሰው መስሎ ወደ እኔ መጣ ብላ ስትናገር ቅዱስ ጊዮርጊስ «እኔ የአምላክ አገልጋይ እንጂ አምላክ አይደለሁም ብሎ መልሶላታል ።

፪ኛ ቤይሩት በተባለው ቦታ የዚያ አገር ሰዎች ለዘንዶ አንዳንድ ልጅ እየገበሩ ያመልኩት ነበር ከእለታት አንድ ቀን አንዲት ቤይሩታዊት ቆንጆ ለዘንዶ ግብር እንድትሰጥ ወላጆች ወስደው ከዛፍ ላይ እንዳደረጉአት ቅዱስ ጊዮርጊስ በዚያ አልፎ ሲሔድ ለምንድር ነው ከዚህ ከዛፍ ላይ የተቀመጥሽው ብሎ ቢጠይቃት ለዘንዶው ግብር ትሰዋለች ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤሩታዊትን ያረጋጋና አይዞሽ ይላታል

ሰዓቱ ሲደርስ ዘንዶው እንደለመደው ግብሩን ሊቀበል ሲመጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ በክርስቶስ ስም አማትቦ ዘንዶውን አንገቱን አስሮ ቤይሩታዊትን እያስጎተተ ወደ ከተማ ገብቶ ይህ እናንተ ስታመልኩበትና ሰው ስትገብሩለት የነበረው አውሬ ከንቱ ነው ራሱን ማዳን አይችልም እያለ በማስተማሩና ገቢረ ተአምራት በመሥራቱ ያየው ሕዝብ ሁሉ በክርስቶስ ስም እንዲያምን አድርጓል።

ከዚያ በኋላ ቅ/ ጊዮርጊስ ልዩ ልዩ ሥቃያትንእየተቀበለ ሰባት ዓመት ወንጌልን አስተምሯል።በእነዚህ ሰባት ዓመታት ውስጥ የተቀበላቸውን ሥቃያት ዘርዝሮ አንድ ባንድ ለመጻፍ ባይቻልም ለ ማስረጃ ያህል ጥቂቶቹን እጠቅሳለሁ ።

ሀ - በዚያ ሀገር የታወቀ አትናትዮስ የሚባል አንድ መሠርይ መድኃኒተኛ ሰው ነበርና መርዝ በጥብጦ አጠጥቶ ጊዮርጊስን እንዲገድል ከዱድያኖስ ትእዛዝ ደርሰው ይህም መሠርይ ከመቅጽበት የሚገድለውን መርዝ በጥብጦ አምጥቶ ቢያጠጣው ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ቀረ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለስብከተ ወንጌል መድቦ በላካቸው ጊዜ « የሚገድል መርዝ አይጎዳቸውም » ብሎ የተናገረው ቃል በቅዱስ ጊዮርጊስም ትርጓሜ አግኝቷል ። ማር . 16 ፡ 18

አትናትዮስ የሚባለው መሠርይ መርዙን ለቅዱስ ጊዮርጊስ በጥብጦ ከአጠጣ በኋላ ምንም ጉዳት እንዳልደረሰበት ተመልክቶ በቅዱስ ጊዮርጊስ አምላክ አምኖና ተጠምቆ የወንጌል መልእክተኛ ለመሆን በቅቷል ።

ለ - በዚህ ጉዳት ሳያደርስበት ቢቀር ይህ ዓላዊ መጋዝ አሠርቶ ሥጋው በዚያ እንዲቆራረጥ ከአደረገ በኋላ አጥንቱን ጨምሮ አስፈጭቶ ደድራስ ተራራ በነፋስ እንዲዘራ አድርጓል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ መላው የሕይወት ዘመን 27 ዓመት ሲሆን ሰባቱን ዓመታት ያሳለፋቸው ልዩ ልዩ መከራ እየተቀበለ ወንጌልን በማስተማር ነበር ሰማዕቱ ቅ ጊዮርጊስ ሚያዚያ 23 ቀን አንገቱን በሰይፍ በተቆረጠ ጊዜ ለተጋድሎው ምስክሮች የሚሆኑ ሰባት አክሊላተ ክብር ከፈጣሪ ዘንድ እንደተሰጡት ገድሉ ይናገራል ።

ወደ ገጽ ጽ፩ ዞሮአል



www.ethiopianorthodox.org

# ማርቆስ ሐዋርያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት
ን በጥንተ ስብከት ሂዱና ለፍጥረቱ ሁ
ሉ ወንጌልን አስተምሩ ብሎ አዘዛቸው።
በትእዛዙ መሠረት ሐዋርያት ሁለት ሁ
ለት ሆነው ከ፸ አርድእት ጋራ ዕጣ በዕ
ጣ ብለው በየሀገረ ስብከታቸው ተሠማ
ርተዋል ። እንደዚሁ ሁሉ ቅ/ ማርቆስ
ም በዕጣ እስክንድርያ ደርሳዋለች ። የ
ቅዱስ ማርቆስ አባት አርስጦቦሎስ ይባ
ላል፣ እናቱም ማርያም ትባላለች የማር
ቆስ የመጀመሪያው የልጅነት መጠሪያ
ስሙ ዮሐንስ ይባል ነበር ። የማርቆስ
አባት አርስጦቦሎስና በርናባስ ወንድ
ማማቾች ነበሩ ቆላ ፬ ፡ 14 ። እነርሱም
በአባት እንጂ በእናት አይገናኙም ነበ
ርና አርስጦቦሎስ ከበርናባስ እናት የም
ትወለደውን የበርናባስን እኅት ማርያ
ምን አግብቶ ማርቆስ የተባለውን ዮሐ
ንስን ወለደ ። የአርስጦቦሎስንና የበር
ናባስን ያኅት ወይም የአክስት ልጅ
ኮንኮርድያን (ጴርጴትዋን ) ቅ ጴጥሮስ
አግብቷት ነበር ። ማርቆስም አክስቱን
የጴጥሮስን ሚስት ለመጠየቅ አንዳንድ
ቀን ወደ ጴጥሮስ ቤት ይመላለስ ነበርና
ስለዚህ የክርስቶስን ነገር ከቅዱስ ጴጥ
ሮስ አፍ ሰምቶ አመነ ። ተጠመቀ በኋ
ላም ጌታችን ሰባ ሁለቱን አርድዕት ሲ
መርጥ ማርቆስም ከሰባሁለቱ ጋራ ተቆ
ጠረ አባቱ አርጦቦሎስ ግን ገና አረማ
ዊ ነበር ። ቅ . ማርቆስም ዘአንበሳ ማር
ቆስ አንበሳው ማርቆስ ይባል ጀመር እ
ደዚህም የተባለበትን ምክንያት ጥቂት
እንገልጸለን ከዕለታት አንድ ቀን ከኢየ
ሩሳሌም ተነሥቶ ከአባቱ ጋራ ወደ ዮር
ዳኖስ ወንዝ ሲወርዱ ወንድ አንበሳና ሴ
ት አንበሳ ባንድነት ሆነው ተነሱባቸው
ና ወደ እነርሱ መጡ አርስጦቦሉስም እ
ንበሶቹን ባየ ጊዜ እጅግ ፈራና ተን
ቀጠቀጠ ልጁ ሆይ እኔ ሽማግሌ ስ
ለሆንኩ ሸሽቼ ለማምለጥ አልችል
ም፣ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ እ
ኔን ይብሉኝ አንተ ግን ገና ጎልማ
ሳ ስለ ሆንህ ሸሽተህ ለማምለጥ ት
ችላለህና ራስህን አድን አለው ቅ/ማ
ርቆስም ከአባቱ አፍ ይህን በሰማ ጊዜ
አባቴ ሆይ በስሙ ያመንሁበት ጌ
ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያድነናልና
አይዞህ አትፍራ አለው ። አንበሳቹም
እየገሠገሡ እየተገሩመሙ ወደ እነሱ በቀረ
ቡ ጊዜ ማርቆስ በታላቅ ቃል እየጮኸ
የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክ
ርስቶስ ሰንጥቆ ይገድላችሁ ልጆቻችሁ
ም ይሙቱ ብሎ ረገማቸው ያን ጊዜ ሁለ
ቱም አንበሶች እየተሠነጠቁ ሞቱ ግለ
ገሎቻቸውም የሚመገባቸው አጥተው
እየሞቱ ተገኙ ስለዚህ አንበሳው ማርቆ
ስ ( ማርቆስ ዘአንበሳ ) ተባለ ይላሉ። ብ
ኢ.ቤት የጻፈውን የእስክንድርያን ሊቃነ
ጳጳሳት ታሪክ 38 ኛውን ገጽ ተመልከ
ት የሀገራችን የኢትዮጵያ ሊቃውንት
ግን አንበሳ ለላም ጌታው ነው ጠላቱ ሆኖ
እንዲሠብረው እሱም በግብሰ አምልኮ
ተ ላህምን አጥፍቷልና ። ዘአንበሳ ማር
ቆስ ተባለ ብለው ተርጎመውታል ቀድ
ሞ የታተመውን ትርጓሜ ወንጌል 200
ገጽ ተመ . ። ደግሞ አንበሳ ባገሣ ጊዜ
ድምፁ ከሩቅ ይሰማልና እንስሳት ሁሉ
ይደነግጣሉ ። አራዊት ይገሠጻሉ ፡ ማር
ቆስም በግብፅ ሆኖ የወንጌል ስብከት
በጀመረ ጊዜ የስብከቱ ድምፅ በግብፅ
አውራጆች ሁሉ ስለ ተሰማ አጋንንት
ደንግጠዋል መናፍቃን ተገሥጸዋልና
አንበሳው ማርቆስ ( ዘአንበሳ ማርቆስ)
ተባለ ይላሉ በአባ ጊዮርጊስ ድርሰት ሰ
ዓታት በሚባለው ኩሎሙ ሠራዊት መ
ላእክት መንፈሳውያን በሚለው ውስጥ
ተመ . አርስጦቦሎስም ልጁ ማርቆስ
በአንበሶች ላይ ያደረገውን ታምራቱን
አይቶ ልጄ ሆይ እስከ ዛሬ ልጄ ነበርህ
ከእንግዲህ ወዲህ ግን አባቴ እልሃለሁ
አለው ። ከዚያም በኋላ አርስጦቦሎስ
በክርስቶስ አመነ ወንድሙ በርናባስ ግ
ን አስቀድሞ ስለአመነ ከሰባሁለቱ አርድ
እት ተቆጥሮ ከቅ/ ጳውሎስ ጋር እየሆነ
ሲያስተምር የኖረ ነው የሐዋ- ሥራ ፲፫፥
፩ - ፵፭ አርስጦቦሎስን ም ቅዱስ ጳው
በሮሜ መልእክቱ የአርስጦቦሎስን ሰ
ዎች እንደ፡ት ናችሁ በሉ ብሎ ስሙን
ጠርቶታል ። ሮሜ 16 ቁ 10 ይህ አርስ
ጦቦሎስ አስቀድሞ በአውግስጦስ ቄሳር
ዘመን በሮም አገር ይኖር ነበርና ምናል
ባት ብዙ ወዳጆችና ቤተሰቦች በሮም
አገር ይኖሩት ይሆናል ብሎ ብ እቤት
በጻፈው የእስክንንድርያ ሊቃነ ጳጳሳ
ት ታሪክ 37ና 38 ገጽ ላይ ያስረዳል ።

የገሊላ አውራጃ በሚሆን በቃና ሠር
ግ በሆነ ጊዜ ወይን የሆነውን ውሀውን
እየቀዱ በ6ቱ ጋኖች ከሞሉት አገልጋዮ
ች አንዱ ማርቆስ ነበር ይባላል ። ከትን
ሣኤም በኋላ ሐዋርያት አይሁድን ፈር
ተው በሩን ዘግተው የተቀመጡበትና
ጌታችን በዝግ ቤት ገብቶ ለሐዋርያት
የተገለጠበት የማርቆስ እናት ቤት ነው
ዮሐ 20 ቁ 19 ቅ . ጴጥሮስንም ሄሮ
ድስ በግዞት ቤት ባሰረው ጊዜ መልአኩ
ከግዞት ቤት አውጥቶ መጀመሪያ እየመ
ራ የወሰደው ወደ ማርቆስ እናት ቤት
ነው ። የሐዋ . ሥራ 12 . ቁ . 12 ቅ .ጴ
ጥሮስም ማርቆስን ልጄ ይለው ነበር ።
ምክንያቱም ከላይ እንደ ገለጽነው የማ
ርቆስ አክስት የጴጥሮስ ሚስት ነበረችና
እያስተማረ ስላሳደገው ነው ። 1 ጴጥ .
5 13 ። ወንጌሉንም የጻፈው ጴጥሮስ እ
የነገረው ነው ይባላል ። የተአምረ ኢየ
ሱስ መጽሐፍ ተመ ። ቅ . ማርቆስ በጵ
ንፍልያ ከቅ . ጳውሎስ ጋራ ሳለ መከራ
ቢጸናበት ልጅም ስለ ሆነ ከእሱ ተለይ
ቶ ወደ እናቱ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም ስለ
ተመለሰ ጳውሎስ ተቀይሞት ነበር ። የ
ሐዋ. ሥራ 13 ፡ 13 ከብዙ ጊዜም በኋላ
ጳውሎስና በርናባስ ለስብከት ሲሄዱ በ
ርናባስ ማርቆስን እንደ ገና ለማስከተል
አስቦ ነበር ነገር ግን ከዚህ ቀደም በጵን
ፍልያ ሳለ በመከራው ጊዜ ተለይቶ ስለ
ሄደ ጳውሎስ 2ተኛ ማርቆስን ለማስከተ
ል አልወደደም ። ስለዚህ በጳውሎስና
በርናባስም መካከል ትልቅ መለያ ዬትና
መከፋፋት ተደረገና ጳውሎስ ሲላስን
መርጦ ከእሱ ጋራ ለብቻው ሄደ ይላል
የሐ . 15 ፡ 37 - 41

ሰው ምንም ጻድቅና ደግ ቢሆን ልቡ
ተለዋዋጭ መሆኑ አይቀርምና ቅዱ
ሳን የተባሉ ጳውሎስና በርናባስ እ
ንኳ ከመለያየትና ከመከፋፋት የደረሱ
በት ማርቆስ የበርናባስ የወንድም ልጅ
ስለሆነ በርናባስ ልቡ ለዘመድ ስለ አደ
ላበት ነው እንጅ ቅ . ጳውሎስ ማርቆስ
ስን በማይገባ ተቀይሞታል ብሎ አይ
መስልም ።
ነገር ግን ቅዱሳን ምንም ቢቀያየሙ ደ
ግሞ ስለ እግዚአብሔር ብለው ይቅርታ
ማድረጋቸው አይቀርምና ቅ . ጳውሎስ
በሮሜ ታሥሮ ሳለ ማርቆስን አምጣልኝ
ብሎ ወደ ጢሞቴዎስ ጻፈ ። ጢሞቴዎ
ስም ወስዶ አስታርቆታል በእሥርም
ቤት ሲያገለግለው ነበር 2ኛ ጢሞ 4ቁ11

በ52 ዓ.ም ግን ቅ . ጴጥሮስ በእስያና
በሌሎችም አገሮች እየዞረ ሲያስተምር
ማርቆስንም ወደ እስክንድርያ ( ካይሮ )
ሂደህ አስተምር ብሎ ላከው ማርቆስ
እስክንድርያ በደረሰ ጊዜ ገና ከከተማው
በር ሲደርስ የጫማው ማዘቢያ ( ቶታኑ)
ተበጠሰበት ። በዚህም አዝኖ ሳለ አንያ
ኑ የሚባል ጫማ ሠፊ አለ ብለው ስለ
ነገሩት ወደ ጫማ ሠፊ ሄደ ጫማውንም
እስቲ ሠሩለት ድረስ ቅ . ማርቆስ ባጠ
ገቡ ተቀምጦ የጌታችን የኢየሱስ ክርስ
ቶስን ነገር ይነግረው ጀመር አንያኑም
በዚህ ነገር ደስ ስላለው ወደ ቤቱ ወስዶ
አሣደረው ። በዚህም ምክንያት አስተ
ምሮና አሳምኖ አጠመቀው ከጥቂትም
ወራት በኋላ ዲቁና ሾመው ቀጥሎም ቅ
ስና ሾመው ቅ . ማርቆስም በእስክንድ
ርያ በሌሎችም አፍሪቃ አገሮች በግብ
ጽ አውራጃዎች እየዞረ 8 ዓመት ያህል
ካስተማረ በኋላ አንያኑን ጳጳስ አድርጎ
ሾመው ሌሎችም 3 ቀሳውስትና 7 ዲያ
ቆናት ሾመ በክርስቶስ ያመኑትም ሁሉ
ደስ አላቸው በዚያው በእስክንድርያ ከ
ተማ በባሕር ዳር ቤተ ክርስቲያን ለመ
ሥራት ተጀመረ ።

ነገር ግን ብዙ ጣዖታትን የሚያመልኩ
አሕዛብ ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ በቁጣ
ተነሥተው ማርቆስን ያዙት ። በዚያም
ዘመን ትንሣኤ በሚያዝያ 29 ቀን ውሎ
ነበርና በማግሥቱ በሚያዝያ 30 ቀን አ
ንገቱን በገመድ አሥረው ከተማ ለከ
ተማ እየጎተቱ ገደሉት ። ክርስቲያኖች
ም ሥጋውን ( በድኑን ) አንሥተው ቤ
ተ ክርስቲያን ለመሥራት በጀመሩበት
ሥፍራ ቀበሩት በወንበሩም አንያኑ ተ
ቀመጠ( ተተካ ) ይህ አንያኑም ባለሚስት
ና ባለ ልጆች ነበር ። ስለዚህ ከዚያ ጀም
ሮ እስከ ዛሬ ድረስ እስክንድርያ የማር
ቆስ ወንበር ስትባል ትኖራለች ከዚህ
ቀጥለን ቅ. ማርቆስ ካረፈ በኋላ አሁን
በቅርቡ በ64 ዓ.ም. ሰኔ 18 ቀን የተደረ
ገውን ፍልሰት አስታውሰን ባጭሩ እን
ጽፋለን ቅ.ማርቆስ ካረፈ እስከ 64 ዓ.ም.
ሰኔ 18 ቀን ድረስ 1ሺህ 904 ዓመት
ሆኖት ነበር ዛሬ በ74 ዓ.ም. ግን 1ሺህ
914 ዓመት መሆኑ ነው 2ቱ የቤኒስ ነጋ
ዴዎች የቅ. ማርቆስን ዓፅም በሥውር
ወስደው በቤኒስ ከተማ አስቀምጠውት
እስከ 60 ዓ.ም. ድረስ ኖሯል ።
በዚያም ከተማ 1ሺህ ዘመን ያህል እንደ
ተቀመጠ የሮሙ ፓትርያርክ ፓፓ ፓል/
6ተኛው ጳውሎስ ዓፅሙ ወደ ጥንታዊ
ሥፍራው ወደ ምድረ ግብፅ እንዲመለስ
አደረጉት ያን ጊዜ ከ80 አገሮች የተላኩ
1ሺህ 251 የቤተ ክርስቲያን አባሎችና
እንደራሴዎች በብዙ መቶ ሺህ ደሚቆ
ጠሩ ምዕመናን በካይሮ ተገኝተው ከቤኔ
ስም ወደ ካይሮ መጥተው የቅ.ማርቆስን
በዓለ ፍልሰቱን አክብረው ውለዋል
ሲል አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰኔ 18 ቀን
64 ዓ.ም. ጽፎ አዘክሮ አስተላልፎታል
ይኸው ዛሬ 10 ዓመቱ መሆኑ ነው ።

አባ ቸርነት ጋሻው በዛ

## ጸሎተ ሐሙስ

ከገጽ ፲፬ የዞረ

መስዋዕት አድርጎ እንደሚያቀርብ አስ
መልክቶ የመጨረሻውን ራት ከበላ በ
ኋላ እንጀራውን አንስቶ አመስግኖ ቆ
ርሶም ሰጣቸውና ስለ እናንተ ነገ የሚ
ሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው ይህንን ለመታ
ሰቢያየ አድርጉት እንዲሁም ጽዋውን
አንስቶ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ ነገ የሚፈ
ሰው ደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው ሲ
ል አዲሱን ሥርዓተ ቁርባን የሠራበ
ት አዲሱን ሕግ የደነገገበት ዕለት ነው

ይህ ብቻ አይደለም ጌታችን ኢየሱ
ስ ክርስቶስ በጸሎተ ሐሙስ በሥራ የገ
ለጻቸው መንፈሳውያን ሥራዎች ሌሎ
ችም አሉ ለምሳሌ የጸሎት ተቀባይና መ
ልስ ሰጭ እሱ ራሱ ሲሆን ጸሎት ለሰ
ው ልጆች ምን ያህል መንፈሳዊ ኃይል
መሆኑን ለመግለጽ የጸሎትን ሥነ ሥር
ዓት ለደቀ መዛሙርቱ ከማሳየቱም በላ
ይ ተግተውና ነቅተው ዘወትር እንዲጸ
ልዩ ትግሁ እንከ ወጸልዩ ከመ ኢትባ
ሉ ውስተ መንሱት ወደ ፈተና እንዳት
ገቡ ተጋኝታችሁ ጸልዩ ሲል አዝዞአቸዋ
ል ማቴ . 26. 41 ።
እንግዲህ በሕማማት ውስጥ ያለው ሐ
ሙስ ጸሎተ ሐሙስ የተባለበት ምክ
ንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተለ
ያዩ መንፈሳውያን ሥራዎች ስለ ፈ
ጸመበት ነው ።

በጸሎተ ሐሙስ የተፈጸሙ መንፈሳ
ውያን ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው
1ኛ የደቀ መዛሙርቱ ን እግር በማጠ
ብ ትሕትናን አስተምሮአል
2ኛ አሮጌውን መስዋዕተ አሪት አሳል
ፎ አዲስ ሥርዓተ ቁርባን ሠርቷል ።
3ኛ/ በጌቴ ሴማኒ ጸለየ
ይህንን አብነት በማድረግ ዛሬ ቀሳው
ስቱ በየዓመቱ በጸሎተ ሐሙስ ቀን በ
ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን ምእመና
ን እግራቸውን ያጥባሉ ይህም ጌታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን ምሳሌ
ነት ለመከተል ሲሆን በሌላም በኩል የ
ዓለም መድህን ክርስቶስ ያሳየውን
ትሕትና ለዘላለም ለማስታወስ ነው ።
በተለይ የማይዙት ፈጣሪ የማይሸሙት
ንጉሥ የማይነቅፉት ጌታ የማይበድሩ
ት ባለጸጋ ሲሆን የደቀ መዛ
ሙርቱን እግር በጉልበቱ ተንበርክኮ ሲ
ያጥብ እ ማየቱ እንዴት ያለ ድንቅ ሥራ
ነው?

እንግዲያስ አምላካችንና መድኃኒታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነቱን ካሳየ
ንና እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም ደ
ግሞ ለሌሎች እንድታደርጉላቸው ሲል
ያዘዘውን ትእዛዝ ተቀብለን በክርስቲያ
ናዊ ሥራ መተርጐም ግዴታችንነው።

ክንፈርግብ ማርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

## የሃምሣ ስድስት ዓመት ጋብቻ

አገርን አገር ከሚያሰኙአት አንዱና ዋነኛው የኅብረተሰቡ መሠረታዊ የኑሮ አቋም ነው ። ማንኛውም ኅብረተሰብ ማኅበራዊ የሆነ የአኗኗር ባህርይ አለው የማኅበረ ሰብእ መሠረቱም ቤተሰብ መሆኑ እርግጥ ነው ። ስለዚህ የአንድ አገር ኅብረተሰብ ሞራሉ ፣ መንፈሱና ሥነ ምግባሩ ያምር ዘንድ በጠንካራ መሠረት ላይ የተዋቀረ ማኅበረ ሰብ ያስፈልጋል ። የማኅበረ ሰብእ ምንጭና መሠረት ቤተሰብ ስለሆነ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ። በተለያዩ አገሮች የተለያየ የቤተሰብ አመሠራረት ሊኖር ይችላል ። ታሪክ ያለው መልካም ማኅበረ ሰብእ መሠረቱ የሆነውን የቤተሰቡን ምንነት ያስረዳል ። በዘፈቀደ የሚመሠረት ቤተሰብ መሠረት የለውምና ውጤቱ ለማኅበረ ሰብእ ጠንቅ ነው ።

በክርስቲያናዊ ጋብቻ ላይ የተመሠረተ ቤተሰብ ለመልካም ማኅበረ ሰብእ ዓይነተኛ መዋቅሩ ነው ። በመሆኑም ክርስቲያናዊና ቅዱስ ጋብቻ በቤተክርስቲያን ሕይወት ብቻ የሚታሰብ ሳይሆን በማኅበረ ሰቡ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ። ሞራለ ጠንካራ ፣ መንፈሰ ቀና ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ፣ ሰውን የሚያከብሩና አገርን የሚወዱ መልካም ዜጐች ከእንዲህ ዓይነቱ ቤተሰብ የሚወለዱ ናቸውና ።

በዚህ ዓምድ የተለያዩ የክርስቲያን ቤተሰቦችን ታሪክ ስናቀርብ መቆየታችን ይታወሳል ። ይህም ትዳር ለያዙም ሆነ ላልያዙ አንባብያን ለአሁኑና ለወደፊቱ ዓላማቸው ጠቃሚ ትምህርት እንደሚሰጥ ይገመታል ። በዚህ ጽሑፍ የቀረበው ቤተ ሰብእ መልካም ምሳሌና አርአያ ሊሆን እንደሚችል በማመን ነው ።

የዚህ ቤተ ሰብእ አባወራ አቶ ዋቅጅራ መርሻ ይባላሉ ። አቶ ዋቅጅራ በ1895 ዓ.ም. ነሐሴ 8 ቀን ከግራዝማች መርሻና ከእመት ወለተ መስቀል ተወለዱ በቤተሰቦቻቸው ሥር በሚኖሩበት ወቅት ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲፈቅድላቸው በዚያን ጊዜ በነበረው የትምህርት ሥርዓት መሠረት ትምህርት ቤት ገብተው ከፊደል መቁጠር እስከ ምንባብ ያለውን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ዕድሜአቸው ለጋብቻ እንደደረሰ ቤተሰቦቻቸው ወ ሮ ወለተ ጻድቅ ወልደየስን ጥቅምት 23 ቀን 1918 ዓ.ም በሀገራችን የጋብቻ ሕግ መሠረት ዳሩላቸው ። ጋብቻቸውን ለምን በሕገ ቤተ ክርስቲያን እንዳልፈጸሙ አቶ ዋቅጅራን ጠይቀናቸው ሲመልሱ በተክሊልና በሥጋወ ደሙ መጋባት የመጣው አሁን በቅርብ ጊዜ ነው ። በዚያን ጊዜ የነበረው በድንግልና መጋባትና በኋላ መቁረብ ነበር ሲያገቡ ሥጋወ ደሙ የሚቀበሉ ዲያቆናት ብቻ ነበሩ ። እኔ ለትንሽ ጊዜ በቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን በዲቁና ባገለግልም በሰገሌ ውጊያ ምክንያት ስለተውኩት የዚህ ዕድል አልገጠመኝም ። ሆኖም ሁለታችንም በተስፋ የምንጠብቀው አብረን ከቆየን በኋላ እንቆርባለን የሚለውን ነበር ። ሲሉ የጋብቻውን አመሠራረት በአጭሩ ገልጸውልናል ።

በዚሁ ሁኔታ በተጋቡ በዓመታቸው የመጀመሪያ ልጃቸውን ወለዱ ። ከዚያም እያከታተሉ የወለዱአቸው ልጆች 12 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 9 ኙ ወንዶች 3 ቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው ። ከነዚህ ልጆቻቸው መካከል ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸውና አንድ ሴት ልጃቸው በሞት ሲለዩአቸው የቀሩትን ዘጠኝ ልጆች ግን እግዚአብሔር ለነርሱ የባረከላቸው መሆናቸውን በማመን በሚገባ አስተምረውና አሳድገው ለወግ ለመዓርግ አብቅተዋቸዋል ።

አቶ ዋቅጅራ ያላሉ ልጆቻችንን ለማሳደግና ቤታችንን ለማስተዳደር በቀድሞው የግቢ ሚኒስቴር ተቀጥሬ አገኘው የነበረው ገቢ በቂ ስላልነበረ እሱን ትቼ ንግድ በሚያመችበት ክፍለ ሀገር እየተዘዋወርኩ አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ መነገድ ጀመርኩ ስለዚህም እንዲያገለግሉኝ ዘጠኝ ያህል የጋማ ከብቶችን ገዛሁ ። በዚህ በቂ መተዳደሪያ አግኝተን





፶፮ ዓመት የጋብቻ ዕድሜ ያላቸው አቶ ዋቅጅራና ወ/ሮ ወለተጻድቅ



እንኳን ለራሳችን ለሰውም ተርፈን መኖር ጀመርን ። እኔ በውጭ ያለውን ሳከናውን ለቤት የሚሆኑትን ሳቀርብ ባለቤቴ ደግሞ ከቤት ልጆቻችንን በማሳደግና ቤትን በመጠበቅ በማዘጋጀትና በመሳሰሉት ሁሉ እየተረዳዳን በመኖር ልጆቻችንን በሚገባ አሳድገናል ። ከዚያም ወዲያ የልጆቻችንን ማደግና እራስ መቻልም ስለመጣ እኔም ብዙ ከወዲያ ወዲህ ባልሯሯጥም ባለሁበት ቦታ ሆኜ ባገኘነው የገቢ ምንጭ መተዳደር ጀመርን ። አሁንም በዚያው እንኖራለን ። እንጂ ልጆቻችንን እርዱን ጡሩን ብለን አናስቸግራቸውም ።

ዛሬ እነሱም የእኛን የቤተሰቦቻቸውን አርአያና ፈለግ በመከተል ሁሉም የየራሳቸውን ቤተሰብ መሥርተው በተለያዩ ክፍላተ ሀገርና በአዲስ አበባም በመኖር እራሳቸውንና አገራቸውን ይረዳሉ ። እነርሱም ያስገኙአቸው የቤተሰቦች ብዛት 36 ደርሰዋል እንግዲህ እኛም አሁን ቅድመ አያቶች ሆነናል ማለት ነው ። እኔም እሷም በሕይወት እያለን እነዚህን ፍሬዎች እንድናይ ስላበቃን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና የማያቋርጥ ነው ።

አሁን ከባለቤታቸው ጋር የሚኖሩበት ሁኔታ እንዴት እንደሆነ አቶ ዋቅጅራን ለጠየቅናቸው ሲመልሱ ቀድሞ ሥርዓቱ ባይፈቅድልንም አብረን ከቆየን እንቆርባለን የሚል ተስፋ ነበረንና ይህንን ተስፋችንን እግዚአብሔር አስፈጽሞን ይኸው በሥጋወደሙ ከተወሰን አሁን 36ኛ ዓመታችንን ይዘናል ። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባው ብለዋል።

በተጨማሪም አሁን ስለአሉበት የቤተሰብ ሁኔታ ጠይቀናቸው ሲመልሱ በቤተሰብእ መካከል እንድንኖር እግዚአብሔር ፈቃዱ ስለሆነ ልጆቻችንን ሁሉ አድርሰን እራሳቸውን አስችለናል ብንልም አሁንም የምንኖረው በቤተሰቦች መካከል ነው ። እነዚህም የልጆቻችን ልጆችና የቤተሰብእ ልጆች የሆኑ ከ14 በላይ የሚሆኑ አሁንም እናስተዳድራለን ። በዚህም ሁሉ እኛ ችግር የለብንም ። እግዚአብሔር ይመስገን በዚህም እንደሰታለን በጋብቻ ኑሮአችንን መሥርተን መኖር ከመጀመርን በት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለኑሮአችን እንጥራለን እንጂ ጥል ቀርቶ አለመግባባትም በቤታችን ተፈጥሮ አያውቅም ። ኑሮአችን ሰላምና ፍቅር የተሞላ ነው ።

የልጆቻችንንም የአኗኗር ሁኔታ እንደምናየው መልካም ምሳሌ የሚታይበት ነው ። ይህም ከኛ ከቤተሰቦቻቸው የወረሱት እንደሆነ አይጠረጠርም ። እኛ ከምናወርሳቸው ነገሮች የሚበልጠውን የአኗኗር ሥርዓት ስለወረሱልን እንደሰታለን ለወደፊቱም በዚሁ እንዲገፉበት ምኞታችንና ጸሎታችንም ነው ።

ደግሞም የብዙዎቹን ልጆቻችንን አካሄድ ስናየው ከእኛ ብዙ ያልተለያየ በመሆኑ በዚሁ መዝለቃቸውን አንጠራጠርም ። ሲሉ አቶ ዋቅጅራ ስለቤተሰቦቻቸው ያላቸውን አስተያየት ገልጠውልናል ።

ይህም ለአንባብያን ሁሉ በምሳሌነቱ ይጠቅማል ተብሎ ይገመታል ። አቶ ዋቅጅራ በአሁኑ ጊዜ የ78 ዓመት አዛውንት ናቸው ። እስከዚህ ዕድሜአቸው ድረስ ያሳለፉአቸው የቤተሰብ አኗኗር ለእራሳቸው አስደሳች ለሌሎች ሰዎች ደግሞ በምሳሌነት ሲጠቀሱ ካሳለፉአቸው ኑሮአቸውና አሁንም እስከቤተሰቦቻቸው ካሉበት ሕይወት ብዙ አርአያነት የሚገኝበት ነው ።

የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ተፈጠረበት ዓለም እስኪመለስ ድረስ ሊፈጽማቸው የሚገቡ የፈጣሪ ድንጋጌዎች አሉት ። እነዚህን ሁሉ መፈጸም ደግሞ የኑሮና የሕይወት ዓላማ ነው በዚህ ሁኔታ ኑሮአቸውን ከገፉት አባቶቻችንና እናቶቻችን የወደፊት ኑሮአችንን ዕቅድ የምንተልምበትን መንገድ ማወቅ ብልህነት ነው ።

## በጎጃም ክፍለ ሀገር

ከገጽ ፳፫ የዞረ

ለፈችው ሴት ልጅ አባትየው አራት አዳዲስ መቀነቶችን ይሸልማታል ። ከዚያም የፍየሉ ሥጋ ተዘጋጅቶ ግብዣው ይካሄዳል ።

ሻንቅሎች ተቀራርበው የሚኖሩ አብረው የሚሰሩ አብረው የሚበሉ ናቸው ። የሚወዱትን ሰው በቋንቋቸው ወዳጅ ብለው ይጠሩታል ። በአንድ እቃ መጠጣታቸው ራሱ አንድነትን ይገልጻል ። የሻንቅላ ብሔረሰብ አባላት ተደሳቾች ናቸው የደመቀ የሙዚቃ ስልት ያማረ የውዝዋዜ ኪነት አላቸው ከቀንድ ከከበሮና ከመሳሰሉት የሙዚቃ ቁሳቁሶች የተበጁት መሣሪያዎች ለሙዚቃዎቻቸው ድምቀት ምክንያቶች ናቸው።

ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት የመተከል ሻንቅሎች እንደሌሎቹ ሁሉ የተረሱ ብሔረሰብ ነበሩ ስለሆነም ትምህርትና መሰል የሥልጣኔ ፍንጣቂዎች ሳይደርሱዋቸው ቆይተዋል ። ስለዚህ በአድሃሪ ባህልና ልምድ ታስረው ቆይተው ነበር ።

አሁን ግን በልማትም ሆነ በመሠረተ ትምህርቱ ዘመቻ ሰፊ እድል ተሰጥቶአቸው በመሳተፍ ላይ ናቸው ። ከአጉል ባህል ተላቀው በኑሮአቸውም የተሻለውን እንዲይዙ የንቃቱ ተግባር ተጠናክሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል ።

## ሰባት ዓመት እንደ ......

ከገጽ ፲፮ የዞረ

እንግዲህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ « ጻድቁን በጻድቅ ስም የተቀበለ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል ።» ብሎ እንደተናገረው በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የምናከብረው በዓልና የምንሰጠው ስጦታ ዋጋ እንደሚያስገኝልን እናምናለን ።

ስለዚህ የቅዱስ ጊዮርጊስ የሰባት ዓመት ተጋድሎ በክርስቶስ ስም ስለሆነ እንደ አንድ ቀን አልቆጠረውም ሲል ደራሲው ቅ/ያሬድ እንደተናገረው ሁሉእኛም በክርስቶስ ስም ስለእውነትና ስለ ጽድቅ የተጋደሉትን ሰማዕታት እናከብራለን አሠረ ጽድቃቸውንም እንከተላለን ።

ነቅዓ ጥበብ ወንድም



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

መልአከ ኃይል ኃይለ ሥላሴ ወልደ ሐና ከአባታቸው ከአለቃ ወልደሐና ከ እናታቸው ከወ/ሮ ማርዬ በ1868ዓ.ም በሸዋ ክፍለ ሀገር በደብረ ብርሃን ሥላሴ አካባቢ ተወለዱ ።

በአባታቸው ቤት ንባብ ከተማሩና ዳዊት ከደገሙ በኋላ ወደሰላ ድንጋይ ተዛውረው ፀዋትወ ዜማን እንዲሁም ቅኔ ከነአገባቡ ተማሩ ።

ከዚያም የኢትዮጵያ ቤተ ርስቲያን ሊቃውንት መናኸሪያ ወደነበረው ና በ ታሪክ ወደታወቀው በወሎ ክፍለ ሀገር ወደሚገኘው ቦሩ ሜዳ ሔደው የቅኔ ት ምህርታቸውን ከአጠበቁ በኋላ ወደአ ዲስ አበባ መጥተው የመጻሕፍተ ብ ሉያትን ትርጓሜ ከመልአከ ብርሃን ተ ክሌ ተማሩ ቀጥሎም ወደ ጎጃም ክ ሀገ ር ተጉዘው ስመጥሩ ሊቅ ከነበሩትከአ ሊቃ ገብረ ኤልያስ ዘንድ ትርጓሜ ብሉ ያትን ለሁለተኛ ጊዜ በሚገባ ተምረው ለመምህርነት በቁ ።

የመንፈሳዊ አገልግሎት ሥራታቸው ወይም ምድባቸው በእንጦጦ ቅዱስራ ጉኤል ደብር ስለነበረ ጸሐፌ ትእዛዝ ገ ብረ ሥላሴ የዚህ ደብር አስተዳዳሪ በነ በሩበት ወቅት የኢትዮጵያን ሊቃውን ት ቅኔ ሰብስበው ለማሳተም በነበራ ቸው ዕቅድ ሁኔታውን በቅድሚያ ለ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ካስገ ነዘቡአቸውና ስለአሠራሩ በአሳብ ከተግ ባቡ በኋላ መልአከ ኃይል ኃይለ ሥላሴ ም በዚሁ ተግባር እንዲተባበሩ አድር ገው በሁለት ባለአደራዎች ማለት በብ ላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና በመልአ ከ ኃይል ኃይለሥላሴ ትጋት አንድ ሺህ አንድ መቶ የሚሆን የኢትዮጵያ ሊቃ ውንት ቅኔ ተሰብስቦ በ1918 ዓ.ም. ታ ትሟል ።

ከዚህ በኋላ መልአከ ኃይል በአዲስ አ በባ ከተማ የተማሩትን ትርጓሜመጻ ሕፍት ጉባኤ ዘርግተው በሰፊው በማስ ተማር ላይ ሳሉ የሲራክና የሰሎሞንን መጻሕፍት የአንድምታ ትርጓሜ ለኅትመ ት እንዲያዘጋጁ ታዝዘው በሚገባ አዘጋጅ ተው ታትሟል ሊቁ የአዲስ አበባ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም መልአከ ኃይል ተብለው የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ደብር አስተዳዳሪነት በየተራ የተ ሾሙ ከመሆናቸውም በላይ ቀደም ብሎ በትምህርታቸውና በአስተያየት ይዘታ ቸው ተመርጠው በወንጀለኛ ቅጣት ፍ ርድ ቤት የፍርድ ሥራ ይሠሩ እንደነበ ረ ተረጋግጧል ።

አስቀድሞ ግፈኛው ፋሽስት ኢትዮጵ ያን በግፍ በወረረበት ጊዜ በኢትዮጵ ያ ሊቃውንት ተመርጠው በኋላም ከነፃ ነት በኋላ ተፈቅዶላቸው የመንፈሳዊ ጉባኤ አማካሪ በመሆን ሠርተዋል ። መልአከ ኃይል በትርጓሜ መጻሕፍ ት ረገድ ከነበራቸው ልዩ ተሰጥዎና የ መራቀቅ ችሎታ ጋር በቅኔ ሞያቸው የ ታወቁና የተመሰገኑ ስለነበሩ ቀጥሎ የ ተመለከተውን መወድስ ለሆሣዕና በ ዓል ተቀኝተዋል ።

መወድስ

ዕብነ ሆሣዕና ተነሥአ ለአፈ ጉባኤ ጽድቀ ሆሣዕና ይትናገር ወበነገሩ ከመ ይጽደቅ
እስመ በነገር ይጠበብ እምነዘካርያስ ሊቅ
እንዘቦ ልሂቅ ዕብነ ጽዮን አ.ይትናገር ሥርዓተ ቅዳሴ ይሁዳ ደቂቅ ።
ወጥንተ ነገር ይጠይቅ ፡ቀዳሚሆሙ ለ ሰብእ ዕብነ ደብረ ዘይት አማሌቅ
መላእክትሂ ተጋቢዖሙ ውስተ ጉባኤ ረቂቅ
እስከ ደመናት አብጽሕዎ ለነገረዕብን ሊቀ ምርፋቅ
ወይብልዎ ን በር ማዕከሌነ ለዕርቅ
አምጣነ አልሐቀ ሆሣዕና ኪያከ አፈወ ርቅ
ከመትኩን ምዕተ ህንተ መልአከ ውዱ ቅ አምጣነ አልሐቀ ሆሣዕና ኪያከ አፈ ወርቅ

ትርጓሜው፡- የሆሣዕናን እውነት ተና ግሮ በነገሩ ይረታ ዘንድ የሆሣዕና ድን ጋይ አፈጉባኤ ሆኖ ተነሣ ። ከሊቁ ከዘካር ያስ ይልቅ ነገር ዐዋቂ ነውና ይኸውም ሽማግሌው የጽዮን ድንጋይ ሳለ የቅዳሴ ን ሥርዓት ልጅ የሆነው ይሁዳ እንዳይ ናገር ነው ።

የጥንቱን ነገር ይረዳ ዘንድ የሰዎች መጀመሪያ የደብረ ዘይት ደንጊያ አማሌ ቅ ነው መላእክት በረቂቁ ጉባኤ ውስጥ ተሰብስበው የሊቀ ምርፋቅ ድንጋይን ነገር እስከ ደመናት አደረሱት ።

ስለወደቀው አንድ መልአከ መቶ ት ሆን ዘንድ አንተን አፈወርቅን ከፍ ከፍ አድርጓልና ለዕርቅ ከመካከላችን ተቀ መጥ ይሉታል ።

በትምህርት በማስተማር በመንፈሳ ዊ ሹመት በፍርድ ሥራና መጻሕፍትን ተርጉሞ በማሳተም እንዲበዛና ለሕዝብ እንዲናኝ በማድረግ ዕድሜያቸውን ለቁም ነገር ብቻ ያዋሉት ሊቁ መልአከ ኃይል ኃይለ ሥላሴ ወልደ ሐና በ1955 በተወለዱ 87 ዓመታቸው አርፈው በአ ዲስ አበባ መካነ ሕይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል።

ከአለቃ አምደ ጽዮን ተሰማ

## ጴጥሮስ በስቅላት ...

ከገጽ ፲፭ የዞረ

ሐዋርያው ጴጥሮስ ዶሮ ሳይጮህ ሦ ስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የክርስቶስ ቃል ትዝ አለውና ወደ ውጭ ወጥቶ መ ራር የሆነ ልቅሶ አለቀሰ ፤ ንስሐ ገብቶ ወደ ፈጣሪው ስላለቀሰ ከክርስቶስ ዘን ድ ይቅርታን አገኘ ይቅርታ ከተደረገለ ትም በኋላ እንደቀድሞው የክርስቶስ ደ ቀ መዝሙር ሆኖ አገልግሎቱን ቀጥ ሏል ።

ተከታዩ ወደ ገጽ ፭ ዞሯል



# በጎጃም ክፍለ ሀገር ስለሚገኙ ብሔረሰቦች

የጎጃም ክፍለ ሀገር በምሥራቅ ከወ ሎና ከሸዋ በምዕራብ ከሱዳን በሰሜን ከጎንደር በደቡብ ከወለጋ ክፍላተ ሀገር ይዋሰናል ። ጎጃም ሰባት አውራጃዎች ያሉትና በደን በዱር አራዊት በወንዞች ና በልዩ ልዩ ማዕድናት የተፈጥሮ ሀብ ት የታወቀ ክፍለሀገር ነው በዚህ ክፍለ ሀገር አማራ ፣ ኦሮሞ ፣ አገው ሽናሻ ሻን ቅላ ቅማንትና ወይጦ የተባሉ ብሔረ ሰቦች ይገኙበታል ።

በዚህ ጽሑፋችን ስለሽናሻና ስለ ሻን ቅላ ብሔረሰቦች ባህል ባጭር ባጭሩ እ ንመለከታለን የሽናሻ ብሔረሰብ በጎጃ ም ክፍለ ሀገር በተለይም በመተከል አ ውራጃ በወምበራ በድባጤና በደንጉር ውስጥ ይገኛል ።

የሽናሻ ብሔረሰብ አባላት ጎረምሳው ና ኮረዳዋ የመስቀል በዓል ሰሞን እየተ ሰበሰቡ መዝፈን ይወዳሉ ። የጋብቻም ጽንሰ ሀሳብ እዚሁ ይጀምራል ። ዳንኪ ራው ሲረገጥ በመሃል ጎረምሳው ዐይኑ የሚያርፍባትን ይቃኝና ከተዋወቁ በኋ ላ ከወደዳት ለዘመዶችዋ አማላጅ ይል ካል ከዚያም በአጸፋው የልጅትዋ ወላጆ ች ስለሚያጫት ወጣት ሁኔታ እስቲረ ዱ በቀጠሮ ይሸኙዋቸዋል ። በሌላ ጊዜ የሁለቱም ልጆች ወላጆች ቀርበው ከ ተነጋገሩ በኋላ ጋብቻው ይሰምራል ወ ይም ይፈርሳል ። ከተስማሙ ልጅትዋ በውዴታ ወይም በግዴታ እንድታገባ ትሆናለች ። ችግሩ ከጥሎሹ ላይ ነው ። የልጂትዋ ዘመዶች ያለሃፍረት ወጣቱ እንዲከፍል እስከ ሺህ ብር ይጠይቁት ነበር ከዚህም በስተቀር በጌጣጌጡ ረገ ድ ወርቅ የብር አምባር ፣ የብር መስቀ ል ፣ የብር አልቦና ሌላም ያቀርባል። በ ዘመኑ የሀብታምና የድሃ ቤተሰብ ጋብቻ የሚባልበትም ሁኔታ ነበር ።

ሙሽራዋ በሠርጉ ዕለት በአያሌው ትቆነጃለች እጮኛዋ የወሰደላትን ቀ ሚስ ኩታና ጌጣጌችዋን ታደርጋለች ከወላጆችዋ ቤት እስከተሰናበተች ድረ ስ እህል የምትቀምሰው ለአመል ያህል እንጂ ጠግቦ መብላት አይፈቀድላትም ሙሽራው መጥቶ ሲወስዳት ፊትዋ መ ገለጥ ስለሌለበት በሻሽ ይሸፈናል በኩ ታዋ ላይም ካባ ወይም በርኖስ ትደርባ ለች ።

ሙሽራው ሊወስዳት በሚሄድበት ጊዜ በጥበቡ ላይ ካቦርት ወይም በርኖ ስ ይደርብና በራሱ ላይ ባርኔጣ ይደፋ ል ። በበቅሎ ላይ ተቀምጦ ሲቀድም ጓ ደኞቹ አጅበው ይከተሉታል ። ከልጅ ትዋ ቤት ገብተው ከበሉና ከጠጡ በኋ ላ ሙሽራዋን ተረክበው ሊወጡ ሲሉ የደስታ ማብሰሪያው ጥይት እየተከታ ተለ ይተኩሳል ። ሆ እያሉ እየጨፈሩ ጉዞ ይቀጥሉና ሙሽራው አባት ቤት ሲ ደርሱ አራት አሞሌ ጨው ይዞ ለምርቃ ት ይገባሉ ። ምርቃቱ ይካሄዳል ከአሞ ሌዎቹ ሁለቱ ለአባትና እናት ይሰጣሉ። ሁለቱ ደግሞ ለተቀሩት ቤተዘመድ እን ዲከፋፈሉት ይሰጣቸዋል ።

የሙሽራዋ አባት ለተቀበሉት ከፍተ ኛ ጥሎሽ አጸፋውን ለሙሽሮቹ የሚሆ ኑ አንዳንድ ሽልማቶችን ያደርጋሉ ልጅ ትዋም ቤት በነበረች ጊዜ የፈተለቻቸ ውን ልብሶችና ሌሎችንም ቁሳቁሶች ለጎጆ መውጫ ይዛ ትሄዳለች ።

## የሻንቅላ ብሔረሰብ

በመተከል አውራጃ በሚኖሩ ሻንቅ ሎች ዘንድ ጋብቻ የሚፈጸመው በጥሎ ሽና በልውጫ ነው ። ልውጫ የሚባለ ው አንድ ጎበዝ እህት ካለችው ለሌላዋ ቆ ንጆ ወንድም እህቱን ይሰጥና በለውጥ እርስዋን ያገባል ። ጥሎሽ ከፋዩ የሚጥ ለው ብዙ ፍየሎችንና አንዳንድ እቃዎ ችንም ነው ። ገንዘብ አግኝቶ ፍየሎቹን ለመግዛት እቃም ለማግኘት ጎረምሳው ቁሞ ቀር እንዳይሆን መልፋት አለበት። ወጣቱ የጋብቻው ጉዳይ ከስምምነት ከ ተደረሰለት ወላጆቹ ይደግሳሉ ። በተለ ይም በልጂቱ ቤት ቦርዴ የተባለ ጠላ ይጠመቃል ገንፎ ይገነፋል የፍየል ሥ ጋ ይቀርባል ። ሙሽራው ታጅቦ ከወላ ጆችዋ ቤት ሲቃረብ ከሚዜዎቹ መሃል አንዱ ተመርጦ ወደ ሙሽራዋ ቤት ይ ላካል ሙሽራዋን ጓደኞቹዋ አጅበው ይወጡና ከቤት ጣሪያ ክዳን ላይ ያስቀ ምጧትና አለንጋ ይሰጣታል ሙሽራው ታጅቦ እንደደረሰ ከጣሪያው ላይ ሊያወ ርዳት በልበ ሙሉነት ሲጠጋት በያዘች ው አለንጋ ትገርፈዋለች እርሱነቱን የ ሚያስመሰክረው ግርፋቱን ችሎ አን ጠልጥሎ ከዚያ ጣሪያ መሬት ሲያስረ ግጣት ነው ። የደጋው ቆነጃጅት ከ በር ሁነው « እናስገባም በሩን ሠርገ ኛውን » እያሉ የሚያስቸግሩትን ሳይመ ስል ይቀራል ? ወደጉዳዩ እንመለስና ግ ርፋቱን ችሎ ሙሽራው ሙሽሪትን በእ ጁ ካገባ እሰየው ካልሆነለትም ሌላ ብ ርቱ ካጀቢዎች መሃል ተመርጦ እንዲያ ወርዳት ይደረጋል ። ከአሁን ወዲህ ግ ብዣ ይቀጥላል ። እንዳበቃም ሙሽራ ው መንገድ ይቀጥላል ። ጋብቻው የእህ ት ልውውጥ ከሆነ ይዞ የሚሄደውና ይ ዞ የመጣው ሙሽራ ከመንገድ ሲገናኙ ቆም ብለው እጆቻቸውን በቅቤ አርሰው ሚስቶቻቸውን ጨብጠው ይመራረቃ ሉ ። ኋላ ሚስቶቻቸውን ከእጆቻቸው አስለቅቀው ከወረወሩዋቸው በኋላ ከወ ደቀበት አንስተው እየዘፈኑ ወደየቤታ ቸው ይሄዳሉ ። በየቤታቸው ሲደርሱ የ ደመቀ አቀባበል ይጠብቃቸዋል ።

የመልስ ጥሪ አለ የሙሽራዋ ወላጆ ች ጥሪ ያደርጋሉ ። ተጠሪዎቹ ሲመጡ ከደጅ አንድ ፍየል ታስሮ ይጠብቃቸዋ ል ። ሙሽራዋን ለውጥ ሰጥቶ ያገባ ወን ድም ዋ ጠብመንጃ አጉርሶ ራቅ ብሎ ይቆማል ለርሷ ጦር ይሰጣትና ፍየሉን ትወጋለች ከወጋች ቀድሞ በሌላ ሰው ያልተደፈረች መሆንዋን ካልወጋች ግ ን ቀድም ሲል ህግዋ የተገሠሠ መሆኑን ታመለክታለች ። ሮጣ ፍየሉን ከወጋች ው ግን ይህን ለማስተጋባት ወንድምዋ ጥይት ይተኩሳል ካልተኮሰ ግን ክብሬ ተደፈረ በሚል ዱላ ፈልጋ እያከታተለች ትገርልጠዋለች ። የባህል ፈተናውን ላ

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ

# የግዕዝ ትምህርት

## ትምህርት 6

| | | | |
|---|---|---|---|
| እድ | እጅ | ላዕለ | በ-ላይ |
| ምስለ | ከ-ጋር | ዲበ | በ-ላይ |
| ኀበ | ወደ | ድህረ | በ-ኋላ |
| ቅድመ | በ-ፊት | እንበለ | ያለ በቀር |
| ሀየንተ | ስለ /ፈንታ/ | እም | ከ |
| መንገለ | በኩል ወደ | እምነ | » |

መክሥት፡- ከዚህ በላይ ያጠናናቸውን ቃላት ለማርባት ስንፈልግ መድረሻ ፊደላቸውን ወደ ሐምስ እንለውጣለን ። ለምሳሌ/ አክሥት በምሳሌ/ "ምስለ" "ኀበ" የተሰኙትን ቃላት አሁን እናርባ።

ሀ/

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምስሌየ | ከእኔ ጋር | ምስሌነ | ከእኛ ጋር |
| ምስሌከ | ከአንተ ጋር | ምስሌክሙ /ተባ/ | ከእናንተ ጋር |
| ምስሌኪ | ከአንቺ ጋር | ምስሌክን /አን/ | ከእናንተ ጋር |
| ምስሌሁ | ከእርሱ ጋር | ምስሌሆሙ /ተባ/ | ከእነርሱ ጋር |
| ምስሌሃ | ከእርስዋ ጋር | ምስሌ ሆን /አን/ | » |

ለ "ኀበ" የሚለውን ደግሞ ልክ እንደዚሁ ለማርባት እንሞክር

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኀቤየ | ወደእኔ | ኀቤነ | ወደእኛ |
| ኀቤከ | ወደአንተ | ኀቤክሙ /ተባ/ | ወደእናንተ |
| ኀቤኪ | ወዳንቺ | ኀቤክን /አን/ | ወደእናንተ |
| ኀቤሁ | ወደእርሱ | ኀቤሆሙ /ተባ/ | ወደ እነርሱ |
| ኀቤሃ | ወደርስዋ | ኀቤሆን /አን/ | ወደ እነርሱ |

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ዐረፍተ ነገር ለመሥራት እንድንችል የሚከተሉትን ቃላት እናጥና ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሥያጥ | ገበያ | ንው /ተባ/ | ኑ |
| እም | እናት | ነዓ /አን/ | » » |
| ነዐ | ና | ቀረበ | መቅረብ |
| ሐዊር | መሄድ | መጺእ | መምጣት |
| ንዒ | ነይ | ላእከ | መልእክተኛ /ተላላኪ |
| | | በጺሕ | መድረስ |

## ዐረፍተ ነገር

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዮሐንስ ሖረ ምስለ መስፍን | ዮሐንስ ከመስፍን ጋር ሄደ | ፍቁርኪ መጽአ ኀቤኪ | ወዳጅሽ ወዳንቺ መጣ |
| እምየ ሖረት ኀበ ምሥያጥ | እናቴ ወደ ገበያ ሄደች | ሖረ ኀቤሁ | ወደርሱ ሄደ |
| እኁየ ነዐ ኀቤየ | ወንድሜ ወደ እኔ ና | ቀርበ ኀቤሃ | ወደርስዋ ቀረበ |
| እኅትየ ንዒ ኀቤየ | እቴ ወደ እኔ ነይ | ወልድየ መጽአ ኀቤክሙ /ተባ/ | ልጄ ወደናንተ መጣ |
| አኃዊነ ንው ኀቤነ | ወንድሞቻችን ወደእኛ ኑ | መጽአ ላእከ ኀቤክን /አን/ | መልእክተኛው ወደ እናንተ መጣ |
| አኃቲነ ነዓ ኀቤነ | እቶቻችን ወደእኛ ኑ | ሖረ ላእከ ኀቤሆሙ | መልእክተኛው /ተላላኪው/ ወደ እነርሱ ሄደ ። |
| እኁከ መጽአ ኀቤከ | ወንድምህ ወደ እናንተ መጣ | በጽሐ ላእከ ኀቤሆን /አን/ | መልእክተኛ ወደ እነርሱ ደረሰ |

"ድህረ ፣እንበለ ፣እምነ ፣ሀየንተ የተባሉትን ቃላት ኀበ እና ምስለን" ባረባችሁበት መንገድ አርቡ ።



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ


www.ethiopianorthodox.org